ሕጋዊ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት

የዘውድ ምክር ቤትና የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል
የውስጥ መመሪያ፤ መተዳደሪያ ደንብ፤ ሥርዓትና

ታሪካዊ ሂደት

የካቲት ፲፱፻፺ ዓ. ም.

[February 1998]

እግዚኦ ኩነኔከ ሀቦ ለንጉሥ ወጽድቀከኒ ለወልደ ንጉሥ።
ከመ ይኰንኖሙ ለሕዝብከ በጽድቅ።



በትረ ኃይል ይፌኑ ለከ እግዚአብሔር እምጽዮን።

ዘውድ

የኢትዮጵያ ዓምድ

መግቢያ

ኢትዮጵያ እንደ ቅርብ የአርኬዎሎጂ ግኝቶች አስረጅነት የሰው ልጆች መፈጠሪያ ቦታነቷ እየተመሠከረ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ዕፀዋት አዕዋፍ እንስሳትና የተፈጥሮ ፈዋሽ ፍልውሀዎች መኖራቸውም ተረጋግጧል። እንደ ቡና ስኳርና ጤፍ የተገኙትና በቅድሚያ የታወቁት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። የእነዚህ ማስረጃዎች ቡና የከፋን ጠ/ግዛት ስም ይዞ «ኮፊ» በመባል ይታወቃል። ስኳርም የመጀመሪያ ግኝታው ከዚሁ ከኢትዮጵያ ለመሆኑ የግዕዝ ስሙን ሦከር «ሹገር» በመባል እስካሁን ይታወቃል። «እመዓር ወሦከር ጥዕመኒ ለአፉዬ።» ሲል የንባብ ማስረጃውም ይገኛል። የሸንኮራ አገዳ ጭማቂ ስለሆነ ዕፀ ሦከር የእንጨቱን ስም ይዞ ቀርቷል። እኒህን ለዓይነት ጠቀስን እንጂ ሌሎችም መነሻቸውና መገኛቸው ኢትዮጵያ ሆኖ ለዓለም የተናኙ የመባልዕት ዕፀዋት የብዙ ብዙ ናቸው።

በሌላ አንጻር ደግሞ ኢትዮጵያ በግሪኮች ዘንድ ትልቅና ስመጥር አገር ናት። ሕዝቧም ተደናቂነት ነበረው።ግሪኮች በየመጣጥፎቻቸው ሁሉ ኢትዮጵ ያውያንን እያደነቁ ጽፈዋል። በተለይም የዓመተ ዓለም ጽሑፎቻቸው ጥሩ ማስረጃዎቻችን ናቸው። በግሪኮቹ የታላቁ አምላክ የዜውስ ልጅ የኢትዮጵያዊቷ ልዕልት ባል እንደነበረና ልጅ እንደወለዱ በአፈታሪክ ጽሑፎቻቸው ተርከዋል። ቀጥለውም ስድስቱን ከዋክብት «አንድሮሜዳ» በመባል የሚታወቁትን የኢትዮጵያ ንጉሣዊ በተሰቦች ናቸው ብለዋቸዋል። ይህን የመሰለው አነጋገርና አተራረክ በዘመኑ ኢትዮጵያውያን የነበራቸውን ታላቅነት አጉልቶ ያሳያል።

ኢትዮጵያ ለአምስት ሺህ ዘመናት መንግሥት መሥርታ በሥልጣኔ ታውቃና ተፈርታ የኖረች አገር በመሆኗ ከሚያደንቁን የሚጠሉን ከሚያከብሩን የሚያንጓጥጡን በዚህ ዘመን በዝተዋል። ለኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ምንጭነት ዋና ማስረጃው ያንድ ኢትዮጵያዊ ቤት ቢታይ ከማምረቻ መሣሪያው እስከ መገልገያ የቤት ቁሳቁሶች ድረስ አገር ሠራሽ ያገር ጥበብ ውጤት ሆነው ይገኛሉ። ናቸውም። ይህ ቢዳብር ቢጎለምስ የጥበብ አገሯ ኢትዮጵያ ነበር። ይህን ሁሉ ብናዳብረው የት በደረስን ነበር? የዚህ ትውልድ የፀፀት እንጉርጉሮ ነው። ኢትዮጵያውያን እግዚአብሔርን አውቀን በአምልኮቱ ፀንተን የኖርን። ክርስትናን ከመጀመሪያዎቹ ከራሳቸው ከሐዋርያት የተቀበልን ነን። ሃይማኖታችን በእግዚአብሔር መልአክ ትዕዛዝ በተዓምር የተሰበከልን ነው። እስልምናም በነቢዩ መሐመድ መዋዕለ ዘመን የነቢዩ የቅርብ ቤተሰቦችን ኢትዮጵያዊ ተቀብላ በሰላም በፍቅር ቦታ ሠጥታ ያውም ክርስቲያናዊው ንጉሥና ሕዝብ ናቸው ይህን

ያደረጉላቸውና የተቀበሏቸው በዚህም ምክንያት ራሳቸው ነቢዩ መሐመድ ለተከታዮቻቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጃቸው መሆኑን በቁራናቸው አስፍረውት ይገኛል። ይህም ሲሆን ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በእግዚአብሔር ፈቃድና በሰላም ለመሆኑ ከላይ የጠቀስናቸው በቂ ማስረጃዎቻችን ናቸው። ይህ ትውልድ የታላቅ ሕዝብ ልጅ መሆኑን የመገንዘብ ግዴታ ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃነትና በእምነት ፀንቶ የኖረ ሕዝብ ነበር። ዘመን አመጣሹ ጥይቱ መትረየሱ ቦምቡ ከአውሮፓላን ላይ እንኳን እየተጣለበት ነፃነቱን አላስቀማም። የዚህ ሕዝብ ትውልድ መሆን እጅግ አድርጎ ያስመካል ያኮራል። ያስደንቃል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አለባበሱ አመጋገቡ አኗኗሩ ሁሉ ታሪካዊ ነው። የማንነቱም መታወቂያ ነው። የሚገርመው ግን ይህን ያህል ዘመን በአንድነት ጠብቆና ተንከባክቦ ያኖረው ዘውድ ነበር። ዘውድ የኢትዮጵያ የአምስት ሺህ ዘመናት መታወቂያና መለያ ታሪካችን ነው። ሕዝብ የመረጠውን ቤተ ክህነት ቀብታ ታነግሣለች። ስለዚህም ይህን ጥምረትና ውሕደት ለማውሳት የተለመደው አነጋገር « ነጋሽ አንጋሽና አስነጋሽ።» በመባል ይታወቃል። የሦስቱ ጣምራነት ያለበት ሥርዓተ መንግሥት ለብዙ ሺህ ዘመናት በነፃነትና በክብር አኑሮን የነበር። ያን ልማድ ያን ፍቅር ዘመኑ በሚጠይቀው ዓይነትና መልክ አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአምልኮተ እግዚአብሔርና በሕግ በተወሰነ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት መለየት አይችልም። ታሪኩና ልማዱ ባሕሉ ያስገድዱታል። የኢትዮጵ ያን ልማትና ዕድገት የሚመኝ ሁሉ ብቸኛ በሩ በታሪኩና በባሕሉ መሠረት ዘውድን ዓርማውና ድባቡ አድርጎ መጓዝ ሲችል ብቻ ነው።

ዘውድ ከጠፋ አምልኮተ እግዚአብሔር ከተደናቀፈና ከሌለ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሆነው ክፉ ቀን ነው። ክፉ ቀንም ጦርነት እርስ በርስ ያለመፈቃቀር ያለመተማመን መገዳደል መዘራረፍ የመሳሰሉት ናቸው። ይባስ ብሎ በመንግሥት ስምኳን የሚያስተዳድረውን ሕዝብ የሚጠብቀውን ወገን በአዋጅ የሚዘርፍና የሚቀማ መንግሥት ወረደበት። በእንዲህ ባለው ዘመንም እንደታየውና እንደምንመሠክረውም የተበላው አያጠግብምም። መሶቡ አይበረክትም። መሬቱም እህል አያበቅልም። ይህንም በተግባር የምናየውና የምንመሠክረው ነው። የክፉ ቀን ትርጓሜውና አፈፃፀሙ ይህ የምናየውና ያሳለፍነው የእልቂት ዘመን ነው። ከዚህ የምንወጣው እኛ ኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን ልጆች መሆናችንን በጥሞና በመገንዘብና በማስተዋል ራሳችንን ካለንና ከነበረን ሥርዓተ መንግሥትና አምልኮተ እግዚአብሔር ውጭ ባለመኖር ነው። ዘውድ በቃል ኪዳን ለኢትዮጵያ የተሠጠ ፀጋ ሕገ እግዚአብሔር ነው። ኢትዮጵያም ሀገረ እግዚአብሔር ናት። ከዚህ ውጭ መኖር እንደማይገባን አውቀንና ተገንዝበን መመለስ ታሪካዊ ግዴታ አለብን። ለዚህም ነው ሦስቱም የታላላቅ ሃይማኖቶች መኖሪያና መከተሚያ ኢትዮጵያ የሆነችው። እነሱም የኦሪት የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ናቸው።

የአገራችን አንድነት የሕዝቡ ሰላም ተጠብቆ በፍቅርና በወድማማችነት ልንኖርና ከየቦታው በዓለም ዙሪያ ከተበታተንበት ሁሉ ተሰባስበን አንድና ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት የምንችለው ባለን በተሠጠን ፀጋ እግዚአብሔር ተጠቃሚዎችና ሕጉን አክባሪዎች ሆነን ስንገኝ ነው። ይህ ደግሞ ሰው ሠራሽ አይደለም። ያለ ምክንያትና ያላንዳች ጉዳይም አይደለም የታቦተ ጽዮን ኢትዮጵ ያ ውስጥ መጥታ መኖር። የክርስቶስ ቀኝ ዕጁ ያረፈበት መስቀል ግሼን ገብቶ

መቀመጥና ሉቃስ የሣላት «ኦሆ በሃሊት ተናጋሪት» በመባል የምትታወቀዋ የሉቃስ እመቤት ኢትዮጵያ መገኘት ሁሉ አገራችን ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አገር በመሆኗ በምርጫ የተሠጣት ፀጋ ነው። ይህ ትውልድ ይህን ዐቢይ ምሥጢር በጽኑ ሊገነዘበውና ሊያስተውለው ይገባል። ዘውድ ለኢትዮጵያ አንድነትና ልማት ፍቅር እንደ ሲሚንቶ ሊያገለግለው የሚችል መንፈሳዊ ፖለቲካዊ ሶሻሊያዊና ኢኮኖሚያዊ መሣሪያው ነው። ይህ ኢትዮጵያዊ ቅርስ በዋዛና በፈዛዛ ልንመለከተውና ልናየው የማይገባ መሆኑን ከታላቅ አደራ ጋር እናስገነዝባለን።

ዘውድ ካለ ታሪካችን ማንነታችን ነፃነታችን ክብራችን ሁሉ አብሮ ይኖራል። ላንድ ሕዝብ ደግሞ ከታሪኩና ከማንነቱ መታወቅና መደነቅ የበለጠ ምድራዊ ፀጋ የለም። በመላው ዓለም የተበተነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ እናት አገሩ የሚሰባሰብበትና አገሩን የሚያበለጽግበት ጊዜና የታሪክ ዘመን መጥቷል። ለመላ ኢትዮጵያውያን ሁሉ አንድነትና ወንድማማችነት የሚሠጠውን ፀጋና ክብር አውቀንና ተረድተን ወደ ልማት ማተኮር ይገባናል። ልማት የሚዳብረውና የሚያሸበርቀው ባገር ላይ ፍቅር ሰላም አንድነት ወንድማማችነትና እኅትማማችነት መሠረት ሲኖራቸው ብቻ ነው። አገራችን በዘልማድ እንደሚነገርላት ብቻ ሳይሆን በርግጥም የዳቦ ቅርጫት ናት። ይህን ግንዛቤ ሠጥተን ወደ ታሪካችንንና ወደ ቀድሞ ክብራችን እንድንመለከት ግንዛቢያችን ይስፋ።

ከዘውድ ምክር ቤት ሰብሳቢ
የተላለፈ መልእክት

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አባት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሕዝባቸውን ወደ ዘመናዊው ዓለም በሥልጣኔ ለማቅረብ ሲሉ ትምህርት የሁሉም ቁልፍ መሆኑን በማመን ዘመናዊ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደረጉት ጥረት የኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ሲያስበው የሚኖር ቋሚ መዘክር ነው። በትምህርት የተገኘውም ዕድገት ኢትዮጵያን ከአሥራ አንደኛው ወደ አሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን እንዳመጣት የብዙ ፀሐፊዎች ብዕር ምሥክርነት ነው። ዘመናዊው ትምህርት ላይ ሲተኮር ብሔራዊው የሥነ ምግባር ወይም የሞራልና የዲሲፕሊን ምንጭ የሆነው ብሔራዊው ትምህርታችንንና ጥበባችንን ትተነውና ጥለነው መጥተናል። ይህም በመሆኑ በእነዚህ ሃያ ሦስት ዓመታት ውስጥ ባገራችን ላይ የደረሰውና የታየው ሁከት ችግር ኃዕርና ጩኸት የሥነ ምግባር ጉድለትና የፍቅረ ቢጽ ሕፀጽ ሁሉ ውጤት ነው። የዚህ ሁሉ በዋና መነሻነት የሚጠቀሰው እንዳባቶቻችን አገርን ወገንን ወላጅንና ታላቅን ማክበርና መውደድን ፈሪሃ እግዚአብሔርን ማወቅና መረዳትን የሚያስተምረው ብሔራዊው ትምህርታችንና ተመክሯችን በዘመን አመጣሽ አስተሳሰብ ተተክቶና ተጥሎ በመጎሳቆሉ ነው።

ባሁኑ ሰዓት ወላጅን ወይንም ታላቅን ማክበር ጓደኛን እንደራስ አድርጎ መውደድ እግዚአብሔርን መፍራት የኋላቀርነት ምልክቶች ሆነው ታይተዋል። ስለዚህም ነፍስ ማጥፋት የሰው መብት መጣስ ሀሰት መናገር ማጭበርበር ከሥነ ሥርዓት ውጭ መሆን ሁሉ የሥልጣኔ ዘርፍ ሆነው በመቆጠራቸው ነው። ኢትዮጵያን ከውጭ ሆነው ሲመለከቷት ወላጆቿን በሞት ያጣች ሁነኛ መጠጊያ ወገን ዘመድ አዝማድ የሌላት ከአውላላ ሜዳ የምትቅበዘበዝን ልጅ ትመስላለች። ግድያው ዝርፊያው ንጥቂያው ጥላቻው ውንጀላው ሁሉ ከአገርነት ደረጃ አውጥቷት ይገኛል።

በሀሰት ከመመሥከር በሀሰት ከመፍረድ የበለጠ የሞራል ኪሣራ ምንም አይኖርም። አንዱን አጥፍቶ ሌላው ለመኖር ብቻ ሲሽቀዳደም ማየት የጥፋት ዘመን ላይ መሆናችን ማረጋገጫ ነው። የሕዝብ አንድነት ያገር ሉዓላዊነት ወደ ጎን ተትተዋል። አንዱ ሲቸገር መርዳት መልሶ ማቋቋም ሁሉ ቀርቷል። በምትኩ እርስ በራሱ መጠላላት ለግል ጥቅም መሞት አገርን በዘር መሸንሸን የጊዜው የፖለቲካ ፋሽን ሆኗል። ሁኔታውን አተኩረው ሲመለከቱት እንደ ባሕር ዓሣ እንዱን ሌላው ሲውጠውና ሲያጠፋው ይታያል። ይህም አፈፃፀም በመንግሥት ደረጃ በመፈፀም ላይ በመሆኑ በሕገመንግሥቱ ጸድቆ የሚሠራበት ነው ያሰኛል።

የሕዝብ መሪ ለመሆን የሥራ ባልደረቦቹን መግደል ያገር ሽማግሌዎችንና የሃይማኖት መሪዎችን ማሠር ምሁራኑን ከሥራና ከኃላፊነት ማባረር ማጥፋት

መሆን የለበትም። ያለመታደል ሆነና ባገራችን ያለው ሁኔታ ይህ ነው። ይህ ደግሞ የአዝመራውን ሰብሳቢዎች አሥሮ መከሩን ሳይሰበሰብ ረግፎ እንዲቀር ማድረግ ነው። አንድ አገር ከአዋቂዎቿና ከሽማግሌዎቿ ተለይታ እንድትኖር ማድረግ ነፍስ የተለየው ሥጋ እንደማኖር ነው። አንድ የውጭ አገር ምሁር ለጥናት ኢትዮጵያ ውስጥ በቆየባቸው ጊዜያት የታዘበውን ሲናገር እንዲህ ብሎታል። «የኢትዮጵያን ሕዝብ ወክለው ባገሪቱ ፓርላሜንት ውስጥ ለአገር ዕድገትና ልማት ይመክራሉ የሚባሉትን የሕዝብ እንደራሴዎች ስናይ በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ምን ቋንቋ ይነገራል? ምን ዓይነት አለባበስ አለ? ብሎ ትርዒት ለማሳየትና ለማሳወቅ የተደረገ ድራማ ነው ከማለት ሌላ ለሥራ ተመርጠው የመጡ ናቸው ብሎ ለመናገር እጅግ ይከብዳል። ላንድ አገር በሚመከርበት ሸንጎ ውስጥ ባንድ ቋንቋኳን ያለመነጋገሩ በእውነት የፈረሰችዋ የባቢሎን ከተማ ነች ብሎ ኢትዮጵያን ከመመሥከር ምንም የሚያግድ ነገር የለም። ባሁኑ ሰዓት የዓለም ሕዝብ ሌት ከቀን ለልማት በሚወደቅበት ሰዓት ያገሪቱን ሸንጎ ማላገጫ ማድረጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመከራ ላይ ለመሆኑ ግልጽ ማስረጃ ነው። ለዚህም ነው ኢትዮጵያ በያመቱ የልመና ስልቻዋን ይዛ የዓለምን ሕዝብ ስትማፀን የምትገኘው። ይህ ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሁሉ የቁም ሞት ነው። ኢትዮጵያ ካሏት የወርቅና ከሌሎች ማዕድናት ባሻገር የማይበቅሉ ቅመሞችና የቅባት እህሎች የሉም። ነገር ግን በአገሪቱ ላይ የሚደረገው ሰው ሠራሽ በደልና ደባ ታሪክ ይቅርታ የማያደርገው ነው። የእያንዳንዱን ባሕልና አነጋገር ፓርላሜንቱ ውስጥ ይዞ ከመምጣት በብሔራዊ ቋንቋቸው ለአገር የሚበጀውን መሥራቱ እጅግ ጠቃሚ ይሆናል።» አዎ! የየሠፈር ቋንቋ መለማመጃ መሆኑን በማዘን ምሁሩ በትዝብት ገልፀውታል። እሱም ብቻ ሳይሆን ያለፉትን መንግሥታት በማውገዝ ያለውን በማወደስ ብቻ ነው ውይይቱም የሚያተኩረው ብለውታል። ይህ ሕዝብና መንግሥት አሠሪና ሠራተኛ ማለት ሕዝብ አሠሪ መንግሥት አገልጋይ መሆኑ ነበር። የሀሳቡም ሆነ የተግባሩ ቅድመ ጽንሰ ኃሳብ የተቀመረው። እንደምናየውና እንደምንሰማው ግን ተገለባብጧል። ከሥልጣን ላይ ለመውጣት መዋጋት ከወጡም በኋላ መውጋት ሲለቁም በጦሩ ተወግቶ ሆነ። የአምስት ሺህ ዘመናት ታሪካችን ተመክሮ ይህን ከመሰለው አሰቃቂ ሂደት እንድንወጣበት ዘወር ብለን አልተመለከትነውም። በዚህ ባሁኑ መልኩና ቅርጹ ሳይሆን ታሪካችን የሚያስተምረን የሕዝብ አገልጋይ ለሕዝብ የሚጨነቅ አገሩን ከወራሪ የሚያድን መንግሥት እንደነበረን ታሪክ ያስተምረናል።

አሁን ካለንበት የፍርሃት የግልምጫና የጡጫ ኑሮስ እንዴት እንውጣ? አገራችን የሽማግሌዎችና የባልቴቶች ደሃ ሆናለች። ወጣቱ ተስፋ የሌለው ሕይወት ላይ ነው። የወደፊት ዕቅድ የለውም። የት እንደሚሄድም አቅጣጫ የሚያሳየውና የሚነግረው አጥቷል። ከጭንቀቱና የሚያደርገውን ከማጣቱ የተነሣ ያገሩን ዳር ድንበር ጥሼ እወጣለሁ ብሎ ከማያውቀው ጫካና በረሀ ገብቶ ብዙ ወጣት የአውሬ ራት ሆኖ ቀርቷል።

ይህን በሕዝብና ባገር ላይ የደረሰ መከራ እንዴት ነው የምናስታግሰው የምንላቀቀውስ? ከዚህ ጭንቀትና መከራ ለመውጣት እንደ ዓይነተኛ ምሳሌ የምንጠቅሳት ጃፓንን ነው። የጃፓን ሕዝብ አንድነት ያገሪቱ ሉዓላዊነት ተጠብቆ ሕዝቧ የዓለምን ገበያ በምርቱ አጥለቅልቆት ይገኛል። የጃፓን ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ተመሳሳይና የቆየ ታሪክ አለው። የአገሪቱ ራስ ንጉሡ ነው።

በሕዝብ በተመረጠ ሸንጎ ወይንም ፓርላማ ትተዳደራለች። የዘውዱ መኖር የአንድነታቸውና የሰላማቸው ዓርማ ነው። መረጋጋት ሰላም ፍትሕ የሕግ የበላይነት ባለበት አገር ልማት ጥበብ ትመረታለች። የኢትዮጵያም ሕዝብ ዘውድ ታሪኩና ቅርሱ ነው። የሰላሙና የመረጋጋቱም ዋስትና ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚያረጋግጠው የኢትዮጵያ ዘውድ የሁሉም ነው። ማን ነው የኔ አይደለም የሚለው? ይህ ሐቅ ነው። ሠላም መሥፈን አለበት። ሕዝቡ ወደ አንድነቱ ወደ ታሪኩ ወደ ባሕሉ መመለስ ይገባዋል። የጠፋውን የወርቅና የዓልማዝ ጌጥ ሲያገኝ በውኑ ደስ የማይለው ማን ነው?

ዘውድ የሌለባቸው ዘመናት በሙሉ የጦርነት የውንብድና የቅሚያና የዝርፍያ ዘመናት ናቸው። ይህን መንገርና ማስረዳት ለቀባሪው እንደማርዳት ይቆጠራል። አንድን ቤተሰብ በሥጋና በደም የተወሐደን ሕዝብ በመልክ በቁመት በጎጥ መለያየት ዲያብሎሲያዊ ተግባር ነው። የሥልጣኔም ሆነ የአንድነት ጠንቅ ነው። እያንዳንዱ መንደር መንግሥት ከሆነች ከታዳሚው አሳላፊው የበዘበት ድግሥ መሆኑ ነው። «እርስ በራሷ የተለያየች መንግሥት ልትፀና አትችልም።» የተባለውም ለዚህ ነው። ጠላቶቻችን በደካማ ጎናችን ገብተው ያገርና የወገን ፍቅር የሌላቸው ሰዎችን መሣሪያ አድርገው የት ላይ እንደጣሉን ፍርዱን ለእያንዳንዱ ኀሊና እንተወዋለን።

ስለሆነም ተስፋ ከመቁረጥ ከጭንቀት ከመከራ ከእጦትና ከድኅነት ጨለማ በአንድነት አሁኑኑ እንውጣ እንላለን። በባሕላችን በማንነታችን እንኩራ። ችግራችንን በጋራ እንወጣው። ሕልውናችን የተመሠረተባቸውን የእርሻ መሣሪያዎቻችንን እናሻሽላቸው። አገራችን የኛ ናትና እያንዳንዱ ዜጋ የሚኖርበት የሚሠራበት የግል መሬት ይኑረው። አልምቶ ዛፍ ተክሎ በፍሬው የሚጠቀምበት ለልጁ የሚያስተላልፈው ሀብት ንብረት ያፍራ። ደክሞ ጥሮ ግሮ ያለማውን የሠራውን ቤት ንብረት የራሱ ብቻ መሆን አለበት። ይህን የመሠለው መብቱ በጽኑ ሕግ መከበርና መረጋገጥ ግዴታ መሆን አለበት። ይህ ካልሆነ ኢትዮጵያዊ መሆን ለገዥዎቹ ብቻ የገንዘብ መበደሪያ የሠነድ ስም ብቻ መሆን ነው።

ስለዚህ ከደረሰብን መከራ ተፀጽተን ተመክረን ወደ አንድነታችን እንመለስ። ወደታሪካችን እንመልከት። ዘውድ የሰላም የብልጽግና የአንድነታችን ዓርማ ነው። በባሕላችን በማንነታችን እንኩራ። ወደ ሰላምና ወደ ፍቅር እንምጣ። ፍቅር ካለን አንጣላም። መከባበር በጋራ መሥራት በጋራ መከበር የፍቅር ምርት ነው። የሁላችንም ወደ ሆነው ለሁላችንም በዕኩልነት ወደምንኮራበት የብዙ ዘመናት ታሪካችን ሳናመነታ ዛሬውኑ እንመለስ። ኢትዮጵ ያ በታሪክ የክብር ቦታ ያላትና ጠላት አሳፍራ የመለሰችው አንድነቷን ይዛ የኖረችው በዘውድ ነው። ለሁሉም ኃያሉ እግዚአብሔር እንዲረዳን እንማፀነዋለን።

ኢትዮጵያ በባሕሏ በታሪኳና በሕዝቧ አንድነት ለዘለዓለም ፀንታ ትኑር።

ልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ
በሕግ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
የዘውድ ምክር ቤት ሰብሳቢ

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፡

ሹመት

ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ. ም.

የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት እንዲከበር የሕዝቡም ደኅንነት እንዲጠበቅ በጠቅላላው ለአገር ዕድገትና ብልጽግና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግት አልጋ ወራሽ በመሆን ከተቀባንበት ጊዜ ጀምሮ ከገናናው አባታችን ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጎን ሆነን አገራችንንና ሕዝባችንን አገልግለናል። አሁንም ጥረታችንና ፍላጎታችን ሁሉ የተጀመረውን ከግቡ ለማድረስ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት ሕይወታችን ደስታው ደስታችን ችግሩ ችግራችን ሞቱ ሞታችን ነው። ከሕዝባችን የተለየ የግል ኑሮ የለንም። እንዲኖረንም አንፈልግም። የምንሻው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠላም አግኝቶ የተደላደለ ኑሮ እንዲኖረው ነው። በታወቀው ምክንያት በሕዝባችን መካከል መሆን ባንችልም በኃሳባችንና በመንፈሳችን ተለይተነው አናውቅም።

በስደት ሆነን መከራውን ችግሩንም አብረን ተካፍለናል። አሁንም በሕዝባችን መካከል በመገኘት ችግሩንና ደስታውን ለመካፈል እንዲሁም መንፈሱን ለማበረታታትና ሞራሉን ከፍ ለማድረግ ኃይሉን አሰባስቦ ታሪካዊ አንድነቱን በማደስ አገሩን በጋራ እንዲገነባ የሚገባንን ሁሉ ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል። ፍላጎታችን እግዚአብሔር እስከ ፈቀደልን ድረስ የተቻለንን ሠርተን ለተተኪው ትውልድ ጽኑ መሠረት በመጣል ታሪካዊ ቅርሳችንን አስረክበን የመሸጋገሪያውን ድልድይ ዘርግተን ለማለፍ ነው። ይህን የቆምንለትን ብሔራዊ ዓላማ በትክክል ግቡን እንዲመታ ለማድረግ ንጉሣውያን ቤተሰብና እንዲሁም አገር አፍቃሪና ለሕዝብ ተቆርቋሪ የሆኑ ታዋቂ ግለሰቦች አብረው እንዲሠሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

ስለዚህ ከዚህ በታች ስማቸው የተመለከተው፤

፩. ልዑል በከሬ ፍቅረ ሥላሴ እንደራሴ
፪. ልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ የዘውድ ምክር ቤት ሰብሳቢ
፫. ልዑል በዕደ ማርያም መኰንን የአገር ውስጥ ጉዳይ ኃላፊ

በመሆን ተመድበው በመመሪያችን መሠረት እንዲያገለግሉ ወስነን ሾመናል።

ፊርማ

ቀዳማዊ ዓምኃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

የዘውድ ም/ቤትና የሞዓ አንበሳ
ዓመታዊ በጀት ዝርዝር መግለጫ

	የወጪ አርዕስት	የወር ወጪ	የዓመት ወጪ
1.	የድርጅቱ አስተዳዳሪ	$3,000.00	$36,000.00
2.	ም/ ሥራ አስኪያጅ	$2,500.00	$30,000.00
3.	የሂሳብ ሹም	$2,000.00	$24,000.00
4.	ጸሐፊ	$1,500.00	$18,000.00
5.	መዝገብ ቤት	$1,500.00	$18,000.00
6.	ሾፌር	$1,200.00	$14,400.00
7.	የቢሮ ኪራይ	$750.00	$15,000.00
8.	ስልክና ፋክስ	$2,800.00	$33,600.00
9.	የመልእክት ሣጥን	$88.00	$88.00
10.	መኪና	$450.00	$25,000.00
11.	ነዳጅ ዘይትና ሰርቪስ	$500.00	$6,000.00
12.	ኮምፒውተርና ማተሚያ	$3,500.00	$3,500.00
13.	የቢሮ ጠረጴዛዎች 6	$7,500.00	$7,500.00
14.	የቢሮ ወንበሮች 18	$9,000.00	$9,000.00
15.	ማባዣ ማሽን	$8,000.00	$8,000.00
16.	የጽሕፈት መሣሪያ	$1,300.00	$15,600.00
17.	የካዝና ገንዘብ/ፔቲካሽ	$500.00	$6,000.00
18.	ለልዩ ልዩ ወጪዎች	$10,000.00	$120,000.00
19.	የጉዞና የውሎ አበል	$10,000.00	$120,000.00
20.	ለጋዜጣና ለመጽሔት	$1,000.00	$12,000.00
21.	ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች	$12,000.00	$144,000.00
	ጠቅላላ ድምር	**$79,088.00**	**$665,688.00**

THE YEARLY PROPOSED BUDGET FOR THE CROWN COUNCIL AND MOA-ANBESSA, ETHIOPIANS FOR CONSTITUTIONAL MONARCHY

Account Name	Expenses in Month	Expenses in Year
1.General Manager	$3,000.00	$36,000.00
2.Vice Manager	$2,500.00	$30,000.00
3.Accountant	$2,000.00	$24,000.00
4.Secretary	$1,500.00	$18,000.00
5.Archieve Technician	$1,500.00	$18,000.00
6.Driver	$1,200.00	$14,400.00
7.Office Rent	$750.00	$15,000.00
8.Tel & Fax	$2,800.00	$33,600.00
9.Mail Box Rent	$88.00	$88.00
10.Car	$450.00	$25,000.00
Fuel, Oil and Service	$500.00	$6,000.00
12.Computer & Printer	$3,500.00	$3,500.00
13.Office Desks 6	$7,000.00	$7,500.00
14.Office Chairs 18	$9,000.00	$9,000.00
15.Coppier Machine	$8,000.00	$8,000.00
16.Stationary	$1,300.00	$15,600.00
17.Peaty-Cash	$500.00	$6,000.00
18.Miscelaneous	$10,000.00	$120,000.00
19.Pardium & Travel	$10,000.00	$120,000.00
20.Newspaper & Magazines	$1,000.00	$12,000.00
21.Branch Offices	$12,000.00	$144,000.00
Grand Total	**$79,088.00**	**$665,688.00**

001
29/4/83

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

H.I.M. Amha Selassie I
Emperor of Ethiopia

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ !

ለብዙ ሺህ ዘመናት በነፃነትህ ፣ በአንድነትህና በታሪክህ ኩርተህ የኖርህና የነበርህ ሕዝብ ነህ ። እጅግ ጥንታዊ የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትና የታሪክ መዛግብት አስደናቂ ታሪክህን ፣ ገናናነትህን ፣ ዕንግዳ ተቀባይነትህንና መልካም ሰውነትህን ሲያወሱልህ ይገኛሉ ።

ከዚያም በመለስ በዘመናዊ ታሪክህ አንድ ነፃ አፍሪቃዊ አገርነትህ ተመዝግቦልሃል ። ከዚያም አልፎ ተርፎ የመላው ጥቁር ሕዝብ መመኪያና መኩሪያነትህ በዓለም ላይ በገሃድ እየተመሰከረልህ ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ !

ትውልድ ያልፋል ትውልድ ይተካል ያገርን ክብር ፣ ያገርን ነፃነት ፣ ያገርን ታሪክ ፣ ያገርን አንድነትና ያገርን ባህል ጠብቆ ለተተኪ ትውልድ ማስተላለፍ ለእያንዳንዱ ዜጋ ብሔራዊ አደራና ክብር ነው ።

እኛን ኢትዮጵያውያንን ከሌሎች እህት አፍሪቃውያን አገሮች ለየት አድርጎ ከሚያሳዩንና ከሚያስደንቁን ነገሮች ውስጥ ለብዙ ሺህ ዓመታት ፀንቶ የቆየው ነፃነታችን ፣ ሥነ ጽሑፋችን ፣ ባህላችንና ሃይማኖታችን ይገኙበታል ። አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ክፍል አብሮ መኖር ባልጠነከረበት ዘመን እኛ ገናና ስሙ-ጥር የሆነ መንግሥት መስርተን እንኖር ነበር ። ይህ ሁሉ ልዕልና ላንድ አገር ምንኛ ታላቅ ክብርና ሞገስ ነው ?

የኢትዮጵያ ግዛት ከቀይ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የተዘረጋ እንደነበር ታሪክ ያስተምረናል ። በታሪካችን ፣ በጠንካራ መንግሥትነታችን ጠላት ሳይደፍረን ፣ ጠላት ሳያሸንፈን ፣ ከዚህ ትውልድ ደርሰናል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ከነገሥታቱ ታሪክ ጋር አብሮ የተዋሐደና የተሠራ ነው ። ይህን ያህል ሺህ ዘመናት በኢትዮጵያ ነፃነት ታሪክ ውስጥ አገራችን ከነገሥታት አልባ ሆና የቆየችበት ዘመን የለም ። ቢኖር የጦርነት ፣ የችግርና የሽግግር ጊዚያቶች ብቻ ነበሩ ። ናቸውም ።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሁላችንም እንደምናውቀው ነገሥታቱ ከመዋዕለ ሕይወታቸውም በኋላ በመልካም ሥራቸው ቅዱስ ተብለው በስማቸው አብያተ ክርስቲያናት ታንፀው እናገኛለን ። ለምሳሌም ያህል ቅዱስ ስብስቲያኖስ ፣ ቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ ፣ ቅዱስ ላሊበላና ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ይገኙበታል ።

ወገኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ !

በአሁኑ ወቅት የምሕረት ፣ የሰላምና ፣ የነፃነት ነፋስ በዓለም ዙሪያ እየነፈሰ ነው ። ያስከተለውም ለውጥ የዓለም ሕዝብ ካሰበውና ከገመተው በላይ ሆኖ ተገኝቷል ። ይህም ነፋስ ጠንካራና ኃይለኛም ሆነ ። በብርታቱም የበርሊንን ግንብ ሰባበረ ። የሁለት ወንድማማች ጀርመኖችን አንድነት አበሠረ ። በደቡብ አፍሪቃ የዘር መድልዎን መዘበረ ። ለምሥራቅ አውሮጳ ነፃነትን ነገረ ።

ይህ የነፃነት ፣ የአንድነት ፣ የሰላም ነፋስ በኢትዮጵያም መንፈስ አለበት ። በኢትዮጵያ ውስጥ እጅግበጣም ሰላም ትፈለጋለች ። ሰላምን ማሥፈን አለብን ። አለባችሁ ። ሠይፍ በመማዘዝ ሰላምን ማምረት አይቻልም ። ከአፎቱ የተመዘዘ ሠይፍ መዛገፉንም ፣ የተመዘዘበትንም ይቆርጣል ። ቀኝ ዕጅ ግራውን ቢቆርጥ ጠላትን ተከላከለ ማለት አይሆንም ። አይደለምም ። የሚሆነው ዕጅን በዕጅ መቁረጥ ነው ። ይህ ደግሞ ራስን በራስ ማጥፋት ወይንም መግደል ነው ።

በውጭ አገር የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ሆይ !

አገር እናት ናት ። እናት መልኳ አያምርም ፣ በኑሮዋ ጉስቋላ ናት ተብላ አትተውም ። እናትን እናት የሚያሰኛት ወላጅነቷ ፣ አስገኝነቷና አሳዳጊነቷ ነው ። አገርም ደኸየች ፣ ተራበች ፣ ሰላሟን አጣች፣ ተዋረደች ፣ ጉሥቁልናዋ አጸየፈ ተብላ የሚሸሿት ፣ የሚርቋትና የሚጠሏት አይደለችም ።

ስለዚህ ለችግሯ በጋራ ፣ ባንድነት መፍትሔ መሻት ፣ ከጉሥቁልናዋ እንድትላቀቅ መርዳት የሁላችንም ጥረት መሆን አለበት ። ይህ ከፍተኛ አደራ ፣ ይህ ከፍተኛ ኀላፊነት ከናንተ ዘንድ እጅግ በጣም ይጠበቅባችኋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ !

ጊዜው ወቅቱ ፣ የሰላም አበባ ፣ የሰላም ፍሬ የሚመረትበት መከር ነው ። ስለ ሰላም ፣ ስለ አንድነት ፣ ስለ እውነት ትጉ ፣ በርቱ ጠንክሩ ።

ሁሉን ነገር ማድረግ የማይሳነው ሕያው እግዚአብሔር ይርዳን ።

ሰላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ቀዳማዊ አምኀ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

H.I.M. Amha Selassie I
Emperor of Ethiopia

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ

===============

ዛሬ ወደ ትላንት ነገ ወደ ዛሬ በመተካት የሦስት ሺህ የነፃነት ያንድነት የታሪክ ዘመናት አሳልፈናል። እነዚህም ዓመታት ብርቅ ድንቅነት ያላቸው ልዩ የታሪክ ቅርሶቻችን ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህን ረጅም ጊዜያት በጥሞና ስንዘክር ምን ያህሉ የደስታ፣ ምን ያህሉስ የመከራ፣ስንቱስ የፈጠራ፣ የመሻሻል፣ የሥልጣኔና የብልጽግና እንደሆኑ ሳንለያይ በጥቅል ነው። ነገር ግን ዘመናቱን ፈልቅቀን በውስጣቸው ያለውን አተኩረን የተመለከትን እንደሆነ እጅግ ብዙ የብዙ ብዙ ፀዋትወ መከራ፣ በደል፣ ጭንቅ እናገኛለን። ያንኑ ያህልም የፈጠራ፣ የብልጽግና፣ የልማት፣ የጀግንነት፣ የፍቅር ያንድነት ክስተቶችንም በጥምሩ እንመለከታለን። ከዚህ ላይ የምንገነዘበው ጉዳይ ቢኖር መዋዕለ ሕይወት ደስታና መከራ እንደቀንና ሌሊት በመፈራረቅ የሚንፀባረቁበት የትርዕይት አደባባይ መሆኑን ነው።

ታሪክ ያንድ አገርን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ግንዛቤዎችን መማሪያ የዕውነትና የገጠመኝ ማስረጃ ነው። እንዲሁም ታሪክ የመማሪያ መጽሐፍ ነው። ብዙ ቁምነገሮችን ማጥናት፣ መገንዘብና መመርመር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ማሳሰብ እንሻለን።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ አሰቃቂ የሚባሉ ዘመናት የጦርነት፣ የሰላም ማጣት፣ የርስ በርስ መጠላላት ከዚያም አልፎ ተፈጥሮ ያስከተላቸው እልቂቶች ሁሉ ተፈራርቀው አልፈዋል። የማይደገሙበት ምክንያት አይኖርም። የታሪክ የሁኔታዎች መደጋገም የተጠበቀ ነውና!

በተለይም ባሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱ የተናጋበት፣ ኑሮው የተወደደበት፣ ሰላሙ የነጠፈበት፣ እጅግ አስጊ አስፈሪና አስደንጋጭ ጊዜ ላይ መገኘቱ ምሥክር የማያሻው ፍፁም እውነት ነው። ይህን ሕዝባዊ፣ ብሔራዊና ታሪካዊ ኃላፊነት ባንድነት፣ በጋራ ቀና ጉዞ ለማስያዝ በተለይ ይህ ትውልድ እጅግ ከፍተኛ አደራ አለበት። ሕዝቡ ባለው የሳይንስ ዕድገት በመጠቀም የዕውቀትን፣ የብልጽግናን፣ ያንድነትን፣ የወንድማማችነትንና ብሔራዊ ጥቅምን በማስከበርና በማዳበር ያካባቢ ተገልጋይና ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስ፣ መሥራት ማበረታታት ተቀዳሚ ግዴታ አድርጎ መውሰድና መቀበል ፍፁም ሕዝባዊ አደራ ነው።

መልካሙና በጎው ነገር ሁሉ ወደ ጎን ተትቶ ራስን በሚጎዳና በሚበድል በንብረትና በሕይወት ላይ ተከታታይና ተደጋጋሚ ጥፋቶችን መፈፀም አካባቢን ማጎሳቆልና የምድር ሲያል መፍጠር ዜጋን የባህል ገሰልተኛ፣ የጤና ጉዳተኛ፣ የድንቁርና እሥረኛ፣ የችግር ምርኮኛ ማድረግ ነው።

ባሁኑ ሰዓት ሲካሄድ የሚታየው ይህ ዓይነቱ መርህ ግብር ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ እርዝተኛ ሆኗል። ኃብት ንብረቱን አጥቷል፣አባት ልጁን፣ ልጅ አባቱን ተለይቷል፣ ከኑሮው ተፈናቅሏል። አካባቢውን ቅዬውን ጥሎ ሸሽቷል በገዛ በራሱ አገር ባይታወር ሆኗል። እንዲህ የኑሮ ምስቅልቅል የወጣበት ጊዜ ቢጠቀስ ያሁኑ ግንባር ቀደም ይሆናል።

ሕዝቡ የሚመኘውን ማግኘት ቀርቶ ያለውን ያጣበት፣ ባገሩ መኖር ያቃተበት የጉስቁልና ዘመን በኢትዮጵያ የተራዘመበት ቢኖር አሁንም ይህ ዘመን ይሆናል። ባሁኑ ወቅት የኢትዮጵያውያን ስደተኞች ቁጥር አራት ሚሊዮን እንደ ደረሰ የሚነገር የጊዜው ነባራዊ ዘገባና ራሱን የቻለ ተቀዳሚ ማስረጃ ነው። አባቶች ሲናገሩ "የመጀመሪያው ስሕተት፣ የሁለተኛው ግን ድፍረት" እንዲሉ ያለፉት የተፈጸሙት የመከ ዓመታት፣ የውጣ ውረድ ጊዜያት ትምህርት ሳይቀሰምባቸው በከንቱ አልፈዋልን? ባለፈው ተጸጽተን ለሚመጣው ተዘጋጅተን፣ አልተቀመጥንም ኖሯልን? እስከ መቼ ኢትዮጵያ የኃሳብ፣ የፀፀት፣ የዋይታ፣ የልቅሶና የሙሾ ማውረጃ አደባባይ ሆና ትኖራለች? ሕዝቡስ እስከ መቼ ድረስ ነው የራሱ ጥላ እያስደነገጠውና እያባነነው የሚኖረው? የሰሜኑ ነፋስ ወደ ደቡብ፣ የምሥራቁ ወደ ምዕራብ በነፈሰ ቁጥር የሕዝቡ መጠለያ ጎጆ መነቃቀል፣ መፈራረስ ይገባዋልን? ይህን የሚያስታግስ፣ ይህን የሚያዋቅር መከላከያ የሚፈጥር ብልሃት፣ ጥበብ፣ ዕውቀት ያለው ሰው የለምን? እስከመቼ ድረስ ይሆን ሕዝቡ ሁለት እግሮች እያሉት የሚያነክሰው? አፍስ እያለው የማይናገረው? እጆችስ እያሉት የማይዳሰሰው? መላ ሕይወትን በፀፀት፣ በዋይታ መጨረስ ይገባልን? እስከመቼስ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞትና በሕይወት መካከል መኖሩን የሚቀጥለው? ይህንስ ኃላፊነት ተረካቢው ማነው? በእውነቱ ትውልድ ያልፋል ትውልድ ይተካል ሲባል የነበረው ትውልድ ያገኘውን፣ ያለውን፣ የነበረውን፣ የሚሻሻለውን አሻሽሎ አጥርቶና አሳምሮ ለሚከተለው ትውልድ ማስረከብ የግዴታ ግዴታው አይደለምን? በባሕላችን መሠረት ይህንስ ካወሳን ዘንድ ባሁኑ ሰዓት፣ ባሁኑ ወቅት ይህንን አደራና ኃላፊነት መወጣት ይገባቸዋል የምንላቸው፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ያገር ሽማግሌዎችና ምሁራን ተቀዳሚ ሲሆኑ፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ዜጋም በስፋትና በጥልቀት የሚጠበቅበት ዐቢይ ብሔራዊ ግዴታና ድርሻም ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢኮኖሚ የፖለቲካና የማኅበራዊ ሞትን በመሞት ላይ ነው። በዜግነቱ ሊያገኘው የሚገባውን፣ ራሱም መልሶ ለአገሩ ሊያበረክተው የሚችለውን ሁሉ መብትም ሆነ ነፃነት አጥቶና ነጥቶ ይገኛል። ይህስ እስከ መቼ ይቀጥላል?

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባህል፣ ታሪክ፣ ወግና ማዕርግ ያለው በዜግነቱ፣ በማንነቱ የሚኮራ፣ እጅግ ሲበዛ ታጋሽ፣ ትሑትና ፈሪሃ እግዚአብሔርን የሚያውቅ፣ ይቅር ባይ፣ ቸር ርኅሩኅና ደግ ሕዝብ ነው። ስለዚህም ነው ኢትዮጵያውያን ዕንግዳ ተቀባዮች ናቸው ተብሎ በዓለም ዙሪያ እንደ ምሳሌ ተጠቅሶ የሚነገርለት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ !

የደረሰብህን መከራና በደል ታግሠህ ከዚህ ደርሰሃል። ይህ ዓይነቱ መራራ ሕይወት ካንተ ጫንቃና ራስ ላይ አሁኑኑ መውረድ አለበት። ጊዜም፣ ፋታም የማይሠጠው ነው። ባንተ ላይ የደረሰው መከራ፣ ችግርና ሥቃይ የዓለምንም ሕዝብ ዓይኖች በዕንባ አጥቧል፣ ልብ ሰቅሏል። ስሜትን ዘግንኗል። ይህ የዓለምን ስሜት ያቆሰለ ብሔራዊ መከራ ቁስል አሁንም ከቶ አላገገመም። እንዲያውም እንደገና ቁስሉ እየተፈገፈገ በመድማት ላይ ነው።

በርስ በርሱ ጦርነት የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ወጣቶች፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት፣ ጧሪ ቀባሪ ያጡ ሽማግሌዎችና ባልቴቶች ቁጥር እጅግ በጣም ብዙ ነው። ምንኛ ያሳዝናል? እጅግ መሪርና ጸጸት ነው። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የደረሰው መከራና ሥቃይ ተነግሮም፣ ተጽፎም እንዲሁ የሚያልቅ አይደለም። ነገር ግን ይህን መከራ፣ ይህን ጸጸት፣ ይህን ሰቆቋው ወደ ደስታ፣ ወደ ብልጽግናና ምሬቱን ጣፋጭ ወደሚደረግበት ተግባር ላይ ማተኮር የሚቻልበትን ሁኔታና ይዞታ ሁሉ ማመቻቸቱ ላይ ጥረት እንዲደረግ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን።

ቂም በቀል ጠፍቶ፣ ልዩነት ተደምስሶ ያንድነት ድምጽ ገኖና ደምቆ የሚሰማበት፣ ወንድማማችነት መተሳሰብና መፈቃቀር በርትቶ ወደ ልማት፣ ወደ ብልጽግና የሚተኮርበት፣ ረሀብ የሚከስምበትን፣ ጦርነት የሚሻርበትን፣ ዜጎች የዕኩልነት፣ የልማት ተካፋዮች የሚሆኑበትን መነጋገሪያ ቋንቋ፣ ማሰቢያ አዕምሮ አድርጎ ለብልጽግና መታጠቅና መሥራት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስሜትና አስተሳሰብ መሆን አለበት። ነገር ግን አሁን እንደሚታየው በነገድ፣ በቋንቋ፣ በመልክዓ ምድር፣ በጥቅሉ በዘር የሚደረገው መከፋፈል ከትክክለኛ አመለካከትና አፈጻጸም ውጭ ነው። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የትውልድ ግንዱን መቁጠር ቢችል አቆጣጠሩ የሚጨርሰው ሰው ሁሉ ካንድ አባት ብቻ የተገኘ መሆኑን ነው። አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለው አኩሪ ያንድነት ታሪኩ፣ ባለው ባህልና ጨዋነት፣ ይቅር ተባባይነት መሠረት ከሁሉም በላይ ለብልጽግና፣ ለልማት ለአንድነት ዕጅ ለዕጅ ተያይዞ መነሳት አለበት። የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን እንደ ዓይን ብሌኑ መጠበቅና እንክብካቤ ማድረግ የሚገባ ዐቢይ ብሔራዊና ዜጋዊ የግዴታ ግዴታ ተቀዳሚ ተግባር መሆኑን እጅግ በጥብቅ ከአደራ ጋር እናስገነዝባለን። አንድነት ኃይል ነው፣ ልዩነት ግን ደካማነት ነውና!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ !

በዕኩልነት፣ በአንድነት፣ በፍቅር ወደ ልማት እንዲገሠግሥ የማድረግ የማሰብ የመሆን አሁንም ሕዝባዊ አደራና ግዴታም ነው። በያካባቢው የተፈጠረውን ማንኛውንም ልዩነት ወደ ኋላ ጥላችሁ በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ወኔ በአንድነት ተነሱ። በያላችሁበት ሰላም፣ ይቅርታ ተባባሉ። ለልማት፣ ለብልጽግና፣ ለአዲስ ሕይወት ተዘጋጁ። በየቦታው፣ በያካባቢው ያላችሁ የሃይማኖት መሪዎች፣ ያገር ሽማግሌዎች ምሁራን ለዕርቅ፣ ለሰላም አስተባብሩ። ይህን አደራና ኃላፊነት ለመወጣት ዝግጁ ሁኑ። የአንድነት፣ የሰላምና የዕርቅ ዓርማን ይዛችሁ ተሠለፉ። የሰላም አርበኞች በመሆን ይህችን ጥንታዊትና፣ ታሪካዊት አገር ከወደቀችበት አዘቅት አውጡ። ይህን ያንድነት ብሔራዊ ጥሪ በእግዚአብሔር ስም ከአደራ ጋር እናስተላልፋለን።

ኢትዮጵያ በሕዝቦቿ አንድነት ለዘለዓለም ኮርታ፣
ደምቃ ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!!

ለሁሉም ኃያሉ እግዚአብሔር ይርዳን

ቀዳማዊ አምኃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

"MO-ANBESSA"

THE CONQUERING LION

በሕግ የተወሰነ ዘውድ
የሞዓ አንበሳ ጉባዔ
በዋሽንግተን ከተማ

ቅዳሜ ሰኔ 22 ቀን 1983 ዓ ም ከሰባት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ድረስ (1:00 - 5:00 PM) በካፒቶል ሒልተን ግርማዊ ቀዳማዊ አምኃ ሥላሴና ግርማዊት መድፈሪያሽ ወርቅ እንዲሁም አልጋ ወራሽ ዘርዐ ያዕቆብ አምኃ ሥላሴ በሚገኙበት ታላቅ ስብሰባ ይደረጋል።

በዚሁም ዕለት ግርማዊነታቸው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ የምሥራች ያሰማሉ።

የዚህ ጉባዔ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ዘላቂ የሆነ ሰላም ለማሥፈንና ዲሞክራሲያዊ የሆነ መንግሥት ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት ሁሉ ዕውን ለማድረግ ሲሆን፣ ኢትዮጵያንም ከጦርነት ወደ ልማት፣ ከረሀብ ወደ ጥጋብ፣ ከድኅነት ወደ ብልጽግና ለማሸጋገርና መፍትሔ ለማስገኘት ነው።

ስለዚህ ይህንኑ ብሔራዊ ጥሪ በማክበር ከጉባዔው አዳራሽ በሰዓቱ እንዲገኙለት ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ ዕደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
የሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል።

ETHIOPIANS FOR A CONSTITUTIONAL MONARCHY
"MO-ANBESSA'
THE CONQUERING LION
INVITES ALL ETHIOPIANS
TO ATTEND ITS INAUGURAL MEETING
AT THE CAPITOL HILTON, ON THE 16TH AND K ST.
ON JUNE 29, 1991 FORM 1:00 PM TO 5:00 PM
HIS IMPERIAL MAJESTY AMHA SELASSIE I,
THE PATRON OF "MO-ANBESSA"
H.I.M. MEDFERIASH WORQ
AND H.I.H. CROWN PRINCE ZERE YACOB AMHA SELASSIE
WILL GRACE THE OCCASION WITH THEIR PRESENCE.

የሞዓ አንበሳ
ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል
አመሠራረትና የሥራ እንቅስቃሴ
ዘገባ

በሻ/ገድሉ ኃይሉ
በዶ/ጌታቸው መካሻና
በለይኩን ብርሃኑ

ሐምሌ 1983 ዓ/፡

(July, 1991)

ማውጫ

===

ርዕስ		ገጽ
	===	==
1.	መግቢያ	i
2.	የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል	
	1ኛ ቃለ ጉባዔ	1
	2ኛ ቃለ ጉባዔ	3
	3ኛ ቃለ ጉባዔ	5
3.	የሞዓ አንበሳ ጉብኝታዊ ሪፖርት ቅጽ 1 በሻምበል ገድሉ ኃይሉ	8
4.	የሞዓ አንበሳ ጉብኝታዊ ሪፖርት ቅጽ 1 በለይኩን ብርሃኑ	17
5.	Summary of the Report By Dr. Getachew Mekasha	25
6.	Budget Requirements	30
7.	Letters to Respected Head of States and Institutions	37

መግቢያ

ይህ ዘገባ ከሞዓ አንበሳ ምሥረታ እስከ አዲስ አበባው የሽግግር መንግሥት መቋቋሚያ ጉባኤ (ኮንፈረንስ) ያለውን ሂደት ያጠቃልላል። ዘገባው በሦስት ዘጋቢዎች የቀረበ ሲሆን በአማርኛና በእንግሊዘኛ የተዘጋጀ ነው። የዘገባውም ዋና ዓላማ ስለ ሞዓ አንበሳ ምሥረታ ከዚያም የሥራ እንቅስቃሴና ሂደት በአጠቃላይ መልኩ ለማቅረብ ነው። የተግባሩ ሂደት ታሪካዊነት ስላለው የሞዓ አንበሳን መነሻ ቃለ ጉባዔ ከዋናው ዘገባ (ሪፖርት) ጋር አያይዟል ይኸውም ታሪካዊ ሂደቱን ያስተካክለዋል ብሎ በማመን ነው።

ሞዓ አንበሳ ታሪካዊና ባላደራነቱን አውቆና ተቀብሎ ሥራውን ሲጀምር የመነሻና የመድረሻ ጣቢያውን አይቶና አውቆ ገምግሞ ነው። ኢትዮጵያ ያላት ታሪክ፣ ባህል፣ ወግና ማዕርግ በጥሩ ሥነ ምግባራዊ ተግባር የተገነባ ከመሆኑም በላይ ከዓለም በፊት የሥልጣኔ ጮራ የፈነጠቀባት፣ ማኅበራዊ ኑሮ የተጀመረባት፣ አብሮ የመኖር ልምድ አብሮ የመሥራት ልምድ የፈረጠመባት፤ ትክክለኛ ሃይማኖት የተመለከባት ጥንታዊው ትምህርት ተወልዶ ያደገባት አገር በመሆኗ ህዝቦቿም የእነዚህ ውጤት አስገኝና ተጠቃሚዎች በመሆናቸው ራሳቸውን ለበጎው ተግባር ሁሉ ያቀኑ ናቸው። ይሁን እንጂ! የመበልፀግን ያህል መደህየት፣ የማደግን ያህል መቀርቀዝ ያለ ነውና! ሁኔታዎች ባስከተሏቸው አንዳንድ ታሪካዊ ምክንያቶች ኢትዮጵያ ከአብዛኛው ያለም ህዝብ ተከልላና ተጋርዳ ብትቆይም ቅሉ ሁኔታዎች በፈቀዱበት በሩ ሲከፈት ወደ ሠለጠነው ዓለም ህዝብ ህይወት ለመቀላቀልና ራስን ለማስተካከል ወደ ተደረገው የሥልጣኔ ግሥጋሤ ከምጥጠንና ከመቸኮል አንፃር ባህላዊው ሥርዓትና ኢትዮጵያዊነት ችላ በመባል የተውሶ ባህል፣ የተውሶ ሥርዓተ መንግሥት፣ የተውሶ ሥልጣኔ፣ የተውሶ ቋንቋ፣ የተውሶ አለባበስ፣ የተውሶ መሣሪያ፣ የተውሶ ዕውቀት ባንድ ወቅት ወይንም በተወሰኑ ዓመታት አንዱ ባንዱ ላይ መጫን በዛ። በረከተ። ይህንኑ ሁሉ ለብዙ ዓመታት ተገልላ የኖረች አገር ማስተናገዱ ከበዳት። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር ቁጣ፣ ትዕግሥት ግጣት፣ እምቢተኛነት እየተፈጠሩና እየተዘወተሩ መጡ። እነሆም የአካባቢውን ሁኔታ መቆጣጠር ጀመሩ። በዚህን ጊዜ ኃይል ቦታውንና አካባቢውን መቆጣጠር ጀመረ። የሁኔታዎች ሁሉ መልክ መለውጥ፣ መጠውለግ፣ የነበረው ባልነበረው መተካት ግድ ሆነ። ይህም ሰላምን በጦርነት ተካ። የህዝቦቹ አንድነት ንርፍ የሸረሸረው ቦይ ሆነ። ከመተሳሰብ መጨቃጨቅ ሠፈነ። ከአንድነት ልዩነት በረታ። ትዕግሥት በቁጣ ተለወጠች። መግባባት፣ መተባበር ከባህላዊው አኗኗር በረገገ፣ መከፋፈል ከመጣ ዘንድ እስከ ዳር ድንበሩ ተባለ። ባኗኗሩ፣ በአቅጣጫ፣ በወንዝ፣ በቋንቋ በሽለቆ፣ በሠፈር፣ በስነጣ ወዘተ.... መገንጣጠሉ ቀጠለ። ጦርነት ዕልቂት ተከተለ ጥፋት ረሀብ፣ ርዛት፣ ጉሥቁልና፣ ድኅነት፣ ስደት ያገሪቱ መታወቂያና መጠሪያ ስም ሆኑ። ሕዝቦችም በተፈጠረው ችግር ሁሉ ተዋጡ። አገሪቷም በተመጽዋችነትና በለማኝነት ታወቀች። ተረጋገጠች። ይህ ነው ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ። ይህን በመከራና በችግር የተለበለበ ፊት እንደገና ለመመለስ የሕዝቦቿ ፍቅር አንድነትና እኩልነት ባህላዊው፣ ልማዳዊው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ኢትዮጵያዊነት መንሠራራት አለበት። ለአምስት ሺህ ዘመናት ባንድነት በሰላም የቆየ ሥርዓት የማይቀጥልበት አንዳችም ምክንያት የለውም።

የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ለማረጋገጥ፣ ሰላምን ለማሥፈን፣ ህዝቡን በዕኩልነት ለመጠበቅ ሕዝ የራሴ ነው የሚለው መንግሥት መመሥረት አስተማማኝ ነው። ስለዚህም ሞዓ አንበሳ ይህን ሕዝቡን በፍቅር አንድነት የሚያስተሳስር፣ በነበረው ባህል፣ ወግና ሥርዓት የሚመራ ሥርዓተ መንግሥት መወለድ አለበት ብሎ የሚያምን ድርጅት ነው። ያለበለዚያ በጉልበት፣ በኃይል፣ በጦርነት ሕዝቡን አንድ አደርጋለሁ፣ አስፈራርቼ እገዛለሁ የሚለው ቋንቋ ከቶ አልሠራም። አይሠራምም። አገሪቱ ያሏት ልምዶች ሁሉ ተከብረውና ተጠብቀው መያዝ አለባቸው። ይህ አስተሳሰብ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አዕምሮ ያለና የሚያንጸባርቅ ገሃዳዊ የተግባር ምኞት ነው።

ሞዓ አንበሳ የኢትዮጵያን አንድነት ሕዝቦቿ በሚፈልጉት በባህላዊው ሥርዓተ መንግሥት እንዲሰባሰቡ እንዲሠሩ፣ እንዲያመርቱ መብታቸውና ባህላቸው ተጠብቆ ከመከፋፈልና ከመጣላት አድማስ ወጥተው እንዲኖሩ የተግባር መርሆው ነው። ይህን አስተሳሰብና ሥርዓት ከጥንት ክብሩ መልሶ ለመትከል፣ መልሶ ወደ ጥንተ ክብሩ ለማስቀመጥ የሞዓ አንበሳ ጥረትና ዓላማ ነው። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥረትና ፍላጎቱም ነው። ይህም ተመስክሯል። ኢትዮጵያዊ በባህሉ፣ በውጉና በማዕርጉ በጨዋነት በሕግ አክባሪነቱ ከሰው ጋር አብሮ ነዋሪነቱን ሁሉ አረጋግጧል። መሻሻል፣ ማድግ፣ ማወቅ፣ መሥራትና ማግኘት የሚፈልግ ሕዝብ ነው። ከእንግዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጦርነትን ማስተናገድ ፈጽሞ አይሻም። አታላይ፣ አጭበርባሪ፣ ተንኮለኛ፣ ዘረኛ፣ ከፋፋይ መንግሥት ፈጽሞ በዓይኑ ማየት አይሻም። ነገር ግን ባንፃሩ የኢትዮጵያን ሰላም፣ አንድነት፣ ባህል፣ ሃይማኖት ባንድነት በዕኩልነት በጠቅላላው ኢትዮጵያዊነትን የሚያበረታ፣ የሚያጎለምስ፣ መንግሥት መፈጠር፣ መከሰት ሕዝቡ እንድሚፈልግና እንድሚያምን ሁሉ ሞዓ አንበሳም ለብዙ ሺህ ዓመታት በተግባር የተፈተነውን ባህላዊውን ሥርዓተ መንግሥት ለመገንባት ታጥቆ የተነሳ ነው። ሞዓ አንባሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስሜትና ፍላጎትን በተግባር ይተርጎም ብሎ የሕዝቡን ምኞትና እምነት ይዞ የሚጓዝ ዙፋናዊው አሰባሳቢ አካል ነው።

ባሁኑ ጊዜ የ2ኛው ዙር ቡድን በአዲስ አበባ የሞዓ አንበሳን ጽ/ቤት ለመክፈት በዝግጅት ላይ ነው። ሞዓ አንበሳ በጥቂት ወራት ውስጥም በሌሎች አምስት ጠ/ግዛቶች ጽ/ቤቱን ለመክፈት በታላቅ ጥድፊያ ላይ ይገኛል።

ሞዓ አንበሳ ያለበትን የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ችግር ለመወጣት በብዙ አቅጣጫ ጥረት እያደረገ ነው። ይህም የአባላት መዋጮን ጨምሮ ያጠቃልላል። ሞዓ አንበሳን በኃሳብ፣ በቁሳቁስና በገንዘብ የሚረዱትን ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ ተቋሞችን ሁሉ ትብብር ይጠይቃል።

ሞዓ አንበሳ ይህን ታላቅ ብሔራዊ አደራ ለመወጣት ታጥቆ ተነስቷል። ያንኑ ያህልም ብዙ ደጋፊዎችና የዓላማው አራማጆች በብዛት አሉት። የብዙኃኑንም ድጋፍ በማግኘት ላይ ነው። ሕዝቡ የሚፈልገውና የሚመኘው ዓላማ በመሆኑ የብዙኃኑን መስተንግዶ እያገኘ ነው። ከዚህ ላይ የሞዓ አንብሳ ጽ/ቤት ማሳሰብ የሚወደው የኢትዮጵያን ብልጽግና ሰላምና ደኅንነት የሚሹ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ያላቸውን ተሳትፎ ያለ ተአቅቦ እንዲካፈሉለት ነው። ሞዓ አንበሳ የፖለቲካ ድርጅት፣ የጎሣ፣ የዘር፣ የሃይማኖት፣ የጾታ የባህል ልዩነት አያደርግም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ አባል መሆን የሚመችልበት ድርጅት ነው።

ቃለ ጉባዔ

=======

ሰኔ 3 ቀን 1991 በዋሽንግተን ቨርጂኒያ ስለ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ የሚወያይ አንድ ኮሚቴ በአስቸኳይ እንዲቋቋም የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ጽ/ቤት ኃላፊ ባወጣው መርሀ ግብር መሠረት የሚከተሉት አባላት የያዘ ጉባዔ ሥራውን ጀመረ። ኮሚቴውም የአገሪቱ ጉዳይ ወደ አስከፊና አሳሳቢ ሁኔታ ላይ በመሄድ ላይ መሆኑን ተገንዝቦ ለዚሁ ጉዳይ ዘላቂና ሕዝብን አንድ የሚያደርግ ሁኔታ እንዲፈጠር አመቺ ግንዛቤውችን እንዲያስተካክል የጉባዔው ዋና ዓላማ ሆኖ ቀረበ።

የጉባዔው ተሳታፊዎች

=============

1. ዶ/ር ጌታቸው መካሻ - ሊቀ መንበር
2. አቶ ነጋ መሥፍን
3. አቶ ቃለአብ ሥግው
4. ሻለቃ ኢያሱ በየነ
5. አቶ ለይኩን ብርሃኑ - የጉባዔው ጸሐፊ
6. ጄ/ፀባይ የማኑ

የስብሰባውን አጀንዳ ለማዘጋጀት ጉባዔው ከአባላቱ የተለያየ መረጃዎችንና አገሪቱ ያለችበትን ሁናቴ አዳምጦ ገምግሟል።

ለጉባዔው ከቀረቡት አንዳንድ መረጃዎች ውስጥ ግንቦት 27 ቀን 1991 እ.አ.አ ለንደን በተደረገው የሰላም ጉባዔ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማስቆጣቱና በአሜሪካኖች ላይም የሚያሳየው ተቃውሞ እጅግ እየበረታ መሄዱንና አዲስ አበባ እንዲገቡና ፀጥታ እንዲያስከብሩ የተደረጉት ወያኔዎች የኢትዮጵያን አንድነት የሚያስጠብቁ ሳይሆኑ የሚያለያዩና ጠባብ ያንድ ብሔረሰብ ስሜትና አስተሳሰብ ያላቸው መሆናቸው መረጋገጡን፤ እንዲሁም በጎጃም፤በጎንደር፤ በሰሜን ሸዋና በወሎ ተቃዋሚው ሕዝብ በእነዚሁ ኃይሎች ላይ መነሳቱንና ጦርነት በማድረግ ላይ መሆኑን። ከዚያም አልፎ ተርፎ ጎጃም ላይ የባህር ዳርን ከተማ፤ ጎንደር ላይ የጎንደርን ከተማ ወያኔዎችን ደምስሶ ነፃ ማድረጉን የመሳሰሉትን መረጃዎች ሁሉ አዳምጧል።

ከዚያም ባሻገር ወያኔዎቹ በደረሱባቸው ጠ/ግዛቶች ሁሉ የአካባቢውን ኗሪ ስሜትና ፍላጎት በማንፀባረቅ በተለይም የንጉሠ ነገሥቱ ወታደሮች ነን። ደርግን ጥለን ንጉሡን ልናመጣ ነው። የሚለውን የሕዝቡን የልብ ትርታ ዜና በማብሠርና ለዕርዳታ የተላከውን ስኳር፣ ዘይትና የእህል ዱቄት ከንጉሡ የተላከ ነው በማለት በመስጠት የሕዝብ መስተንግዶ እየተደረገላቸው አዲስ አበባ እስኪደርሱ ድረስ ያላንዳች ችግር መሄዳቸው መረጋገጡንና አዲስ አበባ ሲደርሱ የአዲስ አበባ ሕዝብ ግን ስለሚያውቃቸው ከፍተኛ ተቃውሞ እንዳደረገባቸው ታይቷል። ማንነታቸው ከታወቀና በተለይም በጎጃም፣ በጎንደር የሕዝብ ንብረት ዘረፋ ማድረጋቸውን ሕዝቡ ሲያውቅ እንደተቃወማቸው በውይይቱ ላይ በሠፊው ተዘርዝሮ ተወስቷል።

ወያኔዎቹ አዲስ አበባም ሲገቡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውርደው የራሳቸውን ቀይ ጨርቅ ማንጠልጠላቸው የኢትዮጵያ ጠላት እንጂ ወዳጆች እንዳልሆኑ አስመስክረዋል።

ጉባዔው እስካሁን ድረስ የንጉሠ ነገሥቱ ጽ/ቤት ያከናወናቸውንና ያደረጋቸውን ተግባራት ዘገባ ካዳመጠ በኋላ የሚቀጥሉትን የመነጋገሪያ አጀንዳ አፀደቀ።

እነሱም፤

1. የጋዜጣዊ መግለጫዎች መቀጠል።
2. የቅስቀሳ ሥነ ጽሑፎች ማዘጋጀትና ማሰራጨት።
3. እንዲሁም የዘውድ ፓርቲ ማቋቋም ናቸው።

ስለ ዘውድ ፓርቲ መቋቋም አስፈላጊነት ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል። በመጀመሪያ የዘውድ ፓርቲ ያስፈልጋል አያስፈልግም በሚለው ውይይት ላይ ከተነሱት ኃሳቦች መካከል ባሁኑ ሰዓት ያሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ ዘውድን እየደገፉ ናቸው ይኸውም "ኢዲኃቅ" አብሮ ለመሥራት ጠይቋል። የንጉሠ ነገሥቱን አስፈላጊነት አምኗል የሚል ኃሳብ ቀርቧል። በተጨማሪም የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አባላቱ ደጋፊነታቸውንም አረጋግጠዋል። ለምሳሌ ከተጠቀሱት የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ኢፒዲኢ(EPDA) "አንድ ኢትዮጵያ" የመሳሰሉት ተጠቅሰዋል። ይህንኑም ኃሳብ ለማጠናከር የንጉሠ ነገሥቱ ጽ/ቤት ለ"ኢዲኃቅ" የማጠናከሪያ ደብዳቤ ጽፏል። ከዚያም በመለስ የኢፒዲኤ ሊቀ መንበር ኮሞዶር ጣሰው ደስታ ከስብሰባው ላይ በመገኘት ደጋፊነታቸውን አረጋግጠዋል።

ይሁን እንጂ ጉባዔው የራስን ሥራ በውክልና ማሠራቱ ብቻ አጥጋቢ ውጤት ስለማያስገኝ ራሱን ችሎ የሚሠራ የዘውድ ፓርቲ መቋቋም አለበት የሚለው ኃሳብ በጉባዔው ተካፋዮች ዘንድ ታምኖበት የስም ማውወጣት ኃሳብ እንዲቀርብ ተጠየቀ።

ይህ ፓርቲም በዓላማው መግለጽ ያለበት የብዙ ፓርቲዎችን መፈጠርና መኖር መደገፍ፤ ነፃ የኢኮኖሚ ይዘትን ማራመድ መሆኑን አስገንዝቧል። ከዚህ ቀጥሎ የፓርቲው ስም ለምርጫ እንዲቀርብ ተጠየቀ።

1. እናት ኢትዮጵያ በአቶ ቃለአብ ሥግው
2. ጥንታዊት ኢትዮጵያ በአቶ ነጋ መሥፍን
3. ኢትዮጵያ ታበጽሕ ኢደዊሃ ኃበ እግዚአብሔር በሻለቃ ኢያሱ በየነ
4. ድል ለኢትዮጵያ በዶ/ጌታቸው መካሻ
5. ሞዓ አንበሳ በአቶ ለይኩን ብርሃኑ

ከነዚሁ ከቀረቡት ስሞች ውስጥ "ሞዓ አንበሳ" የጊዜውን ሁናቴ የሚመለከትና በተለይም ብቸኛ የዘውድ መለያና መታወቂያ ስለሆነ ሥያሜው ተወዳጅና ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ አልፏል። በዚህም የዕለቱ ስብሰባ ተጠቃለለ።

2ኛ ጉባዔ

======

ቀን 6/4/91

ሰዓት 11:00 AM

የስብሰባው ቦታ ኦክተን ቨርጂኒያ

የስብሰባው ተካፋዮች፤

1. ዶ/ር ጌታቸው መካሻ
2. ቀ/ች ባህታ ወ/ዮሐንስ
3. ጄ/ ዓባይ የማኑ
4. አቶ ነጋ መሥፍን
5. ሻ/ ኢያሱ በየነና
6. አቶ ለይኩን ብርሃኑ ናቸው

የዕለቱ አጀንዳ

==========

በ6/3/91 ተወስቶ ካደረው የሚቀጥል ሆኖ

1. ሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል
2. የሞዓ አንበሳ የሥራ ይዘትና ሂደት
3. የሥራ አስኪያጅ ቡድንና መጠን መወሰን

በእኒህ ለዕለቱ በቀረቡት አጀንዳዎች ላይ አባላቱ ውይይት አካሂደዋል።

በተለይም "ሞዓ አንበሳ" የሚለው ስም ከጎረቤት አገሮች በተለይም ከዓረቦች ጋር ያለውን ዝምድና ሊያቃርን ስለሚችል የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል፣ዲሞክራሲና ነፃነት የሚያንፀባርቅ ስም ቢወጣ ይሻላል ተብሎ በሻ/ኢያሱ የቀረበው ተቃውሞ እንዲመዘገብ ጠይቀዋል። ይሁንና ለትግልም፣ ለታሪክም፣ ለነፃነትም እጅግ ተስማሚ ስም በመሆኑ በተለይም የዘውድን ግርማና ክብር የሚያንጸባርቅ ስለሆነ ተቀባይነቱ አመዝኖ ጸድቋል።

ስለዚህ "የሞዓ አንበሳ " ዓላማና ተግባር እንዲዘጋጅ ተወሰነ ሞዓ አንበሳ ፓርቲ ሳይሆን "አሰባሳቢ አካል" እንዲባል ሆኖ የተግባሩም ዘመን በህግ የተወሰነን የንጉሠ ነገሥት መንግሥት አቋቋሞ እንደጨረሰ የአሰባሳቢው አካል ተግባርም ፍጻሜ እንዲሆን ተወስኗል። ቀጥሎም በሞዓ አንበሳ መተዳደሪያ ደንብ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲ አባልን ጨምሮ በአባልነት መመዝገብ መቻሉ ተረጋግጧል።

1. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ህልውና የሞዓ አንበሳ ዋና ጽ/ቤት ከዚሁ ከቤተ መንግሥቱ ሆኖ ሥራውን እንዲያከናውን ሲወሰን፤
2. የሥራ አሥኪያጅ ቡድን ስለመቋቋም፣

የሞዓ አንበሳ የሥራ አሥኪያጅ ቡድን እንዴት ይቋቋም? ስንትስ አባላት ይኑሩት ከየትኛው የአባላት ክፍልስ? ተብሎ የተነሱትን ጥያቄዎች በመመለስ የሥራ አሥኪያጅ ኮሚቴ አባላት ከንጉሣውያን ቤተሰብ ውጭ በሆኑ ሰዎች ቢመራ ከጥላቻና ከመሳሰሉት ይዘቶች ሊያድነው ስለሚችል ከመሃለኛው የኀብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ እንዲሆኑ ስምምነት ተደርሷል። ሆኖም ንጉሣውያን ቤተሰቦች በግል በአንድነት እንዲተሳሠሩና የሞዓ አንበሳ አባላት እንዲሆኑ ተወስኗል።

ከዚህ ቀጥሎ ጉባዔው የሚከተሉትን የሥራ አስኪያጅ አባላት እንዲይገ[ብ] ተስማምቷል። እነሱም፣

1. ሊቀ መንበር
2. ም/ ሊቀ መንበር
3. ዋና ጸሐፊ ና
4. ም/ ጸሐፊ
5. ገንዘብ ያዥ ናቸው

ቀጥሎ ጉባዔው የተወያየባቸው ስለ ሥራ አሥኪያጅ አባላት ምልመላና አመራረጥ ጉዳይ ነበር። ጉባዔው ተመራጭ የሥራ አሥኪያጅ ኮሚቴ አባላት ምርጫ በንጉሠ ነገሥቱ መጽደቅ አለበት በሚለው ኃሳብ ላይ ውይይት አድርጎ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፏል።

1. ተመራጭ የሥራ አሥኪያጅ አባላት ምርጫ በንጉሠ ነገሥቱ መጽደቅ መሾምና መሻር አለበት፤ ይኸውም በመተዳደሪያ ደንቡ እንዲመዘገብና እንዲሠራበት፤

2. ለሞዓ አንበሳ የሥራ አሥኪያጅ አባላት በየቦታው በሚመረጡበት ሁሉ ይህ ቃለ ጉባዔ እንደ ውሳኔ ተጠብቆ ተግባራዊ እንዲሆን፤

ከዚህ በኋላ የጉባዔው አባላት ለዚሁ የሥራ አሥኪያጅ የስም ዝርዝር ለሚቀጥለው ስብሰባ እንዲቀርብ ተወስኖ የዕለቱ ጉባዔ ልክ በ5:00 PM ተፈጽሟል።

3ኛ ጉባዔ

======

ቀኑ ሰኔ 5 ቀን 1991 እ.አ.አ
ሰዓት 10:00 AM

የስብሰባ ቦታ ኦክተን ቨርጂኒያ

የጉባዔው ተካፋዮች

1. ዶ/ር ጌታቸው መካሻ የጉባዔው ሊቀ መንበር
2. ቀ/ች ባህታ ወ/ሥላሴ አባል
3. አቶ ነጋ መሥፍን "
4. ጄ/ ዐባይ የማኑ "
5. ሻ/ ኢያሱ በየነ "
6. አቶ ለይኩን ብርሃኑ የቃለ ጉባዔ ጸሐፊ ናቸው
7. ወ/ሮ ርብቃ ወ/ማርያም ከዕረፍት በኋላ ተጨምረዋል

የጉባዔው አጀንዳ

===========

1. የአባላት ምዝገባ መቀጠል
2. የሥራ አሥኪያጅ ኮሚቴን ምርጫ ማከናወን

እንደተለመደው የዕለቱ ስብሰባ ተጀምሮ የአባላት ምዝገባ ተግባር ቀጠለ፡፡ አሉ የሚባሉትን ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በመፈለግ በቅድሚያ በቨርጂኒያ፣ በዋሽንግተን ዲሲና በሜሪላንድ የሚመገኙትን በአባልነት ብሎም ለሥራ አሥኪያጅ ኮሚቴ ተግባር ይሳተፋሉ የሚመባሉትን በመሻት ምዝገባ ተካሄደ፡፡

ይኸውም ካበቃ በኋላ በካሊፎርኒያ ወደሚገኙት ኢትዮጵያውያን ምዝገባ ቀጥሎ በጠቅላላው 125 አባላትን መዝግቧል፡፡ ይሁንና ከ15 ሺህ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያንን ስም የያዘ ሰነድም ለጉባዔው ቀርቧል፡፡ ይሁንና ጉባዔው የጠ/ጽ/ቤቱን የሥራ መዋቅር ካቋቋመ በኋላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም በየስቴቱ በሚቋቋሙበት ወቅት የተጣራ የአባላት ምዝገባና የሥራ አሥኪያጅ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ላይ መወያየት ጀመረ፡፡

ጉባዔው በዕለቱ የሞዓ አንበሳ ጽ/ቤትን ይመራሉ ተብሎ የታመነባቸውን የአባላት ስም ዝርዝር ማቅረብ ጀመረ። ተወዳዳሪ አባሉ የሥራ ችሎታው ፣ ለሥራው ያለው ፍፁምነትና ና'ገስሰቡ በቂነት (know how commitment and effectiveness) መታየት እንዳለበት ግንዛቤ ተሰጥቷል።

ይህን በመሰለ ሁኔታ ጉባዔው ውይይት ካካሄደ በኋላ የሥራ አስኪያጅ አባላትን ምልመላ ቀጠለ። እነህን አባላት መርጦ ለንጉሠ ነገሥቱ ለማቅረብ የተለያዩ የመምረጫ ጠባያትን ሠፋ አድርጎ ተመልክቷል። በዚሁ መሠረት ይህንኑ የምርጫ ጠባያትን ያሟላሉ የተባሉ የአሥር አባላትን የስም ዝርዝር ቀደም ሲል ለጉባዔው በንጉሠ ነገሥቱ ጽ/ቤት በተሠጠው የሥራ መመሪያ መሠረት ከሠፊ ውይይት በኋላ መርጦ አቅርቧል። የተመራጭ አባላትም የስም ዝርዝር በጉባዔው ከፀደቀ በኋላ ለተመራጭ የሥራ አስኪያጅ አባላቱም ሆነ ለጽ/ቤቱ በግልጽ እንዲታወቁና የሚሰጣቸውንም የሥራ ኃላፊነት በቃለ መሐላ ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ቀርበው እንዲፈጽሙ በውይይቱ ላይ ተወስቷል።

ከላይ የተጠቀሱት አሥር የሥራ አስኪያጅ ተወዳዳሪ አባላት ውስጥ ጉባዔው ተወያይቶ አምስቱን ለሊቀ መንበርነትና ለምክትል ሊቃነ መናብርትነት ሲያሳልፍ አምስቱን ደግሞ ለጠቅላይ ፀሐፊነት፣ ለምክትል ፀሐፊነትና ለዋና ገንዘብ ያዢነት መርጧል።

ይህንኑ የምርጫ ዝርዝር ለንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ እንዲጸድቅ በውሳኔ አሳልፎ ጉባዔው አጠቃላይ የተሠጠውን ተግባር ፈጽሞ ሞዓ አንበሳን መሥርቶ የተጠራበትን የሥራ ተግባር አከናውኖ ስብሰባውን አጠቃሏል።

ይሁን እንጂ የጉባዔው አባላት ያከናወኑትን ዝርዝር የሥራ ዘገባ ለግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት በልዩ ጽ/ቤቱ በኩል አቅርቧል። ጉባዔው የተወያየባቸውን ዝርዝር ተግባራት በአስቸኳይ በሥራ እንዲተረጎሙ ይቻል ዘንድ የሥራውን ኃላፊነት እንዲሠጣቸው የቀረቡት የሥራ አስኪያጅ አባላትም ለሥራው ያላቸውን ፈቃደኝነትና ትጋት ጭምር አብሮ እንዲታይ በውይይቱ ላይ አውስቷል።

ይህንኑ የጉባዔም ውሳኔ በአስቸኳይ በተግባር ላይ እንዲውል አሳሳቢነቱን ገልጾ የተጠራበትን አጠቃላይ ሥራ ፈጽሞ በ3-15PM ላይ የጉባዔው አባሳት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘንድ ቀርበው ተሰናብተዋል።

ከሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል የተሰጠ ቅስቀሳዊና
ጉብኝታዊ ሪፖርት

===========

ሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ ከ07/05 -07/14/91 ዓ/ም ድረስ በመገኘት የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ ያጋጠመውን ከባድ ችግር በመገንዘብና ወደፊትም ሃገሪትዋን ሊያጋጥማት የሚችሉትን አሳቃቂ ሁኔታዎች በግምት ውስጥ በማስጋባት ከኢትዮጵያ ታሪክና ባህል የመነጨና የነበረ ኢትዮጵያዊ መፍትሄ ነው። ከሠፊው ሕዝብ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያደረገውንና ከአንጻሩም የተደረገውን ድጋፍ ከዚህ እንደሚከተለው ተዘርዝሮአል።

ሰኔ 24 ቀን 1983 ዓ/ም (July 1, 1991) ለሚደረገው የሽግግር መንግሥት ዝግጅት ጉባዔ ላይ ለመገኘት በተላለፈው ዓለም አቀፍ ጥሪ መሠረት ግርማዊ ቀዳማዊ አምኃ ሥላሴን ወክለን ለመገኘት እሁድ June 30, 1991 ወደ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ጉዞአችንን በTWA በNew York በኩል ለመሄድ

1. ዶክተር ጌታቸው መካሻ የመልክተኞች መሪ
2. ደጃ.ብርሃነ መስቀል ደስታ መልክተኛ
3. ባላ. በዛብህ አደመ "
4. አቶ ለይኩን ብርሃኑ "
5. ሻምበል ገድሉ ኃይሉ "
6. ወ/ሮ ርብቃ ወ/ማርያም "
7. አቶ ቴዎድሮስ ገብረየስ " ሆነን

ዋሽንግተን ኢንተርናሽናል አየር ማረፊያ እንደደረስንም አየሩ ለ1 ሰዓት ያህል በመዘግየቱ ምክንያት ጠቅላላው በጉዞው በኩል ያለው ግንኙነት ሁሉ ተቃወሰ።

በመሆኑም በቲኬቱ ግዢ አነስተኛ ወጪ በመፈለግ የተገዛ ስለነበረ ለተፈለገው ዓላማችንም ለነበረው ስብሰባ ካለመድረሳችንም ሌላ ተጨማሪ ትኬት በመግዛት ነው አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ከ3 ቀን በኋላ እንኳን ለመድረስ የተቻለው።

አዲስ አበባ ቦሌ ኢንተርናሽናል አየር ማረፊያ በ07/05/91 እንደደረሰን ዕቃችንን አስፈትሸን ከአጠናቀቅን በኋላ እንግዳ መቀበያ (VIP) እንደተቀመጥን የኢሕአደግ አስተናጋጆች ቡናና ሻይ ጋበዙንና ከአስተዳደሩ ወይም ከስብሰባው አዳራሽ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች መጥተው ያነጋግሩአችኋል ተባልን እኛም ለሁለት ሰዓት ያህል ስንጠባበቅ ቆየንና አራት መልዕክተኞች እዚያው እንዲጠብቁና ሁለት መልዕክተኞች ደግሞ ሻንጣችንን በማጓጓዝና ሆቴል በመያዝ ሥራውን ተከፋፈልን በዚህም ወቅት

(የሞዓ አንበሳ) አርማ ቲ ሸርቶች ብዛት 80 ፤ ልዩ ልዩ ምስረታን በሚመለከት የሚገልጽ በ3 የወቀረት ሳጣን ውስጥ የነበሩትን ጽሁፎች በሙሉ በጉምሩክ ተቆጣጣሪ ፈታሾች ተይዘውብናል፤ ብንጠይቅም ከታየ በሁዋላ ይሰጣችሁአል በሚል እልባት ብቻ ለማግኘት አልቻልንም ። ይህም ስነጽሁፍ መያዝ የሚገባ አልነበረም ለተልኮአችንም ዋና መሣሪያ እንደነበረ ግልጽ ነው። የማይሰጠን መሆኑን ከተገነዘብን በሁዋላ የዚሁ ኮፒ በያንዳንዳችን እጅ ስለነበረ በብዛት በማሳተም ለሄድንበት ዓላማና ግብ ዋና አስፈላጊ መሣሪያ በመሆኑ እንዲታደል አድርገናል። ተቀባይነቱም ከፍተኛ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። ግን ቲ ሸርትና ሞዓ አንበሳ አርማ ያለበት አዲስ አበባ ማሳተም አልተቻለም የዚህንም ዓይንት ቲ ሸርትና የአንብሳ ምስል ያለበት እንድናድል በብዛት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢጠይቀንም አሳትመን ለማደል ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የማቴሪያል እጥረት ለጊዜው አልቻልንም።

መልእክተኞችን በሚመለከት ወደ ስብሰባው አዳራሽ አልተገኘንም አልተጋበዝንም በመሆኑም የሄድንበትን ተልእኮ በሕዝቡ አካባቢ በአጥጋቢ ሁኔታ ተወጥተናል በዚህም ጉዳይ ቅስቀሳና ገለጣ የተደረገባቸው መንግሥታዊ መ/በቶች ድርጅቶችና ልዩ ልዩ ግላዊና የሃይማኖት አባቶችና ቤተክርስቲያናትና አድባራት ከዚህ እንደሚከተሉት ተዘርዝረዋል።

1. በካዛንቺዝ አካባቢ (ሕዝብ በብዛት የሚገኝበት)
   ሀ. ግብርና ሚኒስቴር (ከዛአንችዝ ያለው)
   ለ. ቤቶች አስተዳደር ዋና መ/ቤት
   ሐ. ልዩ ልዩ ግለሰቦችና የሃይማኖት አባቶች (በሚገኙበት አካባቢ ሁሉ)
2. አራት ኪሎ አካባቢ
   ሀ. እንደ ወጣት ወንዶች ማህበራዊ ጽ/ቤት
   ለ. ጡረታ ሚኒስቴር መ/ቤት
   ሐ. C.P.A መ. ሠ. ጽ/ቤት
   መ. ትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤት
   ሠ. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
   ረ. አገር አስተዳደር ሚኒስቴር፤ ፖሊስ ሠራዊት፤ ብሄራዊ ትያትር፤ ባህል ሚኒስቴር የባቡር ጣቢያ መሥሪያ ቤት ና ልዩ ልዩ ግለሰቦችን

ስለሞዓ አንበሳ ምስረታ

ስለሞዓ አንበሳ የውስጥ ደንብ

ግርማዊነታቸው ያደረጉትን ንግግር በሚመለከትና እንዲሁም

ጠቅለል ባለሁኔታ የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም የአፈናና የጭቆና አገዛዝ በመወገዱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ድል ነው፤ ይህም ድል የተገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት 17 ዓመታት ባካሄደው መራር የትጥቅና፤ የፖለቲካ፤ እንዲሁም በፊት ለፊትም ሆነ በስውር፤ በመቋቋም ሕዝቡ ባደረገው ታላቅ ትግል ነው ለዚሁም ድል ኢህአዴግ አስተዋጽኦ ማድረጉ ሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል ይገነዘባል።

በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ ሕዝቡ ከፊቱ የተደቀነበት ምርጫ በቅርቡ ታሪክ ውስጥ ከታየው ከማንኛውም ሁኔታ በበለጠ ጐልቶ የሚታይበት ጊዜ መሆኑን ሞዓ አንበሳ ያምናል ይኸውም አማራጭ ከታሪካችን የመነጨ የጋራ ባህል የጋራ ጥቅምና ታሪክ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲ የሆነ እንደ እንግሊዝ፤ ጃፓንና ሲውድን፣ አገር በሕግ የተከለለ ዘውዳዊ አገዛዝ መንግሥታዊ ስርዓት ማቋቋምና መመሥረት ሲሆን፣

በአንጻሩም ጠባብ የሆነ ጐሳዊና ጐጣዊ ጥቅሞችን በመገፋፋት ሕዝባችንን እንዳይከፋፍልና በበለጠ እንዳይደኸይ የሚያደርገውን ሁሉ ነጥቦች በቅድሚያ በመገንዘብ ሕዝቡ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ ሰፋ ባለ ሁኔታ በሚገባ መልክ በማስረዳታችን ከሕዝቡም የተሰጠን መልስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለትም ወጣት፤ ሽማግሌ፤ አሮጊት ሳይል ለሞዓ አንበሳ በሕግ የተከለለ (Constitutional Monarchy) መንግሥት ወደ ተከበረና ታሪካችንም ወደ ሚመሠክርለት ከለላና አቅጣጫ ማምራት ወይም ደግሞ ጉም እያስጨበጠ 17 ዓመታት ያጠፋትና ለእልቂትዋ ያደረሳትን ዓይነት መንግሥት ወደፊት እንዳያስተዳድራት ቢደረግ ኢትዮጵያን እንዳልነበረች አድርጎ የሚያጠፋት መሆኑን መረዳትና በቅድሚያ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የታሪክ ተልዕኮ ሃላፊነት እንዳለበት መረዳት የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው በሚል ከአያሌ ተናጋሪዎች ተሰንዝሮአል ሕዝቡም በጥልቀት የተቀበለው መሆኑን በጭብጨባ አጸፋውን በማያወላውል መልሶአል ወደፊትም ከጐናችን እንደሚቆም አረጋግጦአል።

በመደምደሚያውም ተሰብስቦ የነበረው ሕዝብ በአንድ ድምጽ ዕድሜ ለግርማዊ አምኃ ሥላሴ፤ ዕድሜ ለግርማዊት መድፈሪያሽ ወርቅ ኢትዮጵያችንም ነፃነትዋን ባህሏንና ታሪክዋን ጠብቃ ለዘለዓለም ትኑር በማለት የቀኑ ቅስቀሳና ገለጣ ተጠናቆአል።

በዚህ ቀን በተለይ አንድ ኢንጂነር ለሥራ ጉዳይ ወደ አሰብና ወደ አዋሳ እንዲሁም ወደ ድሬዳዋና ሐረር በመልሱም ጊዜ ወደ ናዝሬትና ወንጅ አካባቢ ማምረቻ ክፍሎችን አንድ ከፍተኛ የጉብኝት ቡድን በመምራት ስለሚዘዋወሩ ገልጸው ያሰሙትና የተደረገውንም ገለጣ አዳምጠው በነበረው በመደገፍ ለሃገራችን አንድነት ታሪክ ባህል ይደርሳልም ተብሎ የሚገመተውን የእርስ በርስ ጦርነቶች እንዳይደርስ ሞዓ አንበሳ ያሰባስባል የሚል ታሪካዊ ልዩ እምነት አሳድሮብኛልና የምንሄደው በቡድን መልክ በመሆኑና እኔም የቡድኑ መሪ ሃላፊ እንደመሆኔ ሁሉ ኢትዮጵያዊ መፍትሄ መፈለግ የአንዳንዳችን ዜጋ ሃላፊነት መሆኑን ሰለማምን ስለሞዓ አንበሳ ምሥረታና የውስጥ ደንብ እና የግርማዊነታቸውን ንግግር በሚመለከት ሁሉ አስፈላጊውን ገለጣና የተሰጠኝንም ጽሁፍ ቢያልቅብን እያባዝን ሕዝቡን አንደ አንድ ካድሬ ሆነን እናስረዳለን በሚል በከፍተኛ ሞራል አረጋግጠዋል።

ሕዝቡም ንግግሩን በመቀጠል ኢትዮጵያ ከብዙ ዓመት በፊት የኖረች ወደ ፊትም የምትኖር ዘውዳዊ አገዛዝ የሰፈነባት ለማንም ቅኝ ገዢዎች ያልተንበረከከች ወደፊትም የማትንበረከክና አሁን እንዳየነው እንዳሰማችሁትና እንደ አነበባችሁልን ለሀገራችን ለኢተዮጵያችን አንድነት ታሪክ ባህል በዓለም የወደቀውን የረከሰውን ስማችንን ለማንሳት ለማሳረም ሞዓ አንበሳ (Constiutitional Monarchy)በሕግ የተከለለ ዘውዳዊ መንግሥት እንድ እንግሊዝ፣ጃፓን፣ስውዲን ዓይንት መንግሥት ቢሆን መልካም ነውና በኛ በኩል አስፋላጊውን አስተዋጽኦ በግንባርም እስከ መሳተፍ ድረስ የሚያደርጉ መሆኑን በማረጋገጥ ስለ ሞዓ አንበሳ የተጻፉትን የምስረታ የውስጥ ደንቦችንና የግርማዊነታቸውን ንግግር በማደል ስብሰባው አብቅቶአል።

በግዮን ሆቴል

============

በግዮን ሆቴል የተሰበሰበው የጎንደር ክፍለ ሀገር ታዋቂና ተደማጭ አዛውንቶችና ወጣቶች በተገኙበት የሞዓ አንበሳ ተልእኮ ምስረታውን በሚመለከት የውስጥ ደንቡንና የግርማዊነታቸውን ንግግር ሁሉ በንባብ ከተሰማ በኋላ ገለጣው ቀጥሎ ከተሰብሳቢዎችም መሃከል የሚሰማቸውንና ለወደፊት ይሆናል ብለው ያመኑበትን ለምሳሌ ሞዓ አንበሳ እንደ አንድ ድርጅት ሆኖ በስብሰባው እንዲካፈልና ወንበር ቢይዝ ለወደፊቱ ምርጫው በሚካሄድበት ጊዜ ከፍተኛ የሕዝብ ድምጽ እንደሚያገኝ አጠራጣሪ አይሆንም ስለሆነም አንድ ከፍተኛ ኃይል በሞዓ አንበሳ አካባቢ ያለውን ጉልበት ስለ ሚያደራጅለት በዚህ መልኩ ቀጥሉበት የሚልና ሌላው ደግሞ ደርግ 17 ዓመታት ሙሉ ታሪካችን እንዲጠፋ ክብራችን እንዲዋረድ ሰድቦ

በማሰደብ ያደረገውን ፕሮፓጋንዳ ትክክል አለመሆኑን ለማስረዳት ለማሳመን የታሪካችን መንስኤ የጎልውናችን መሠረት የአንድነታችን ኃይል ዘውድ እንደነበረም ወደፊትም መሆን እንደሚገባው አብሳሪ ግንባር ቀደም ፋና ነው በሚል የሞዓ አንበሳን ምሥረታ በመደገፍ የገለጡ ከመሆኑም ባሻገር ቀጥሉ ግፉበት ከዚህ በፊት እንደተደረገው ዝግየታ እንዳይደረግ በአዲስ አበባም ሆነ በየጠቅላይ ግዛቱ ይህንኑ የሚመለከት ቀስቃሽና አብሳሪ አስረጂ አካል ማሰራጨት ለሞዓ አንበሳ ምሥረታ ዋና መሠረት ይጥላል ለአንድነታችንም አሰባሳቢ ኃይል ነው። እኛም ሆንን እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ የተለየ ሃሳብና ተልእኮ አይኖረንም በማለት ስለ ምሥረታው የተጻፉትን ሰነዶች በማደል ስብሰባው አብቅቶአል።

የመኢገማ የኢትዮጵያ የገበሬዎች ማህበር መ/ቤት
==================================

ይህ ክፍል ከ7 ሚሊዮን ተኩል በላይ የሆነው የኢትዮጵያን ገበሬ የሚያቅፍ አካል በመሆኑ በኛ በኩል ከፍተኛ ትኩረት ነው ያደረግነው። ምክንያቱም ደርግ 17 ዓመት ሙሉ የገበሬውን ድጋፍ በመሻት ያደርገው የነበረውን ቅስቀሳና ማደራጀት ቀላል አልነበረም የኢትዮጵያንም ሕብረተሰብ በማስጠላትና ታሪክም የለሽ አገር ለማድረግ ከተጠቀመባቸው መንገዶችና ድርጅቶች አንደኛውና ከፍተኛው መኢገማ እንደነበረ ከማንም አይሰወርም ሆኖም በግብርና ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ልዩ ልዩ የዘውድ ደጋፊዎች አማካይነት ከመኢገማ ጽ/ት በመገኘት ስለ ሞዓ አንበሳ ምስረታ ስለ ሞዓ አንበሳ የውስጥ ደንብና ግርማዊነታቸው ያደረጉት ንግግር ሁሉ በንባብና መግለጫ መልክ አስረድተን ጽሁፎችንም አድለናል። በዚህም ወቅት ከያንዳንዱ የመኢገማ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ይሰማ የነበረው ድምጽ ሞዓ አንበሳ ታሪካችን ወጋችን ሃይማኖታችን የአንድነታችን ዓርማ ነው በሚል እየደጋገሙ በማንሳት ደርግ ለራሱ ስልጣን ለመያዝ ሲል 17 ዓመት ሙሉ የአንድነታችን የመታወቂያችን መሠረት የነበረውን የዘውድ አገዛዝ በራሱ ስልጣን ገርስሶ ይሄው የዓለም ሕዝብ መሳለቂያና መሳለቂያ ታሪክ የለሽ ሕዝብና ደሃ አገር አድርጓታል።

በመሆኑም አዲሱ ትውልድ ከዚህ በመነሳት ከሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል ጋር ጉልበቱንና ሕይወቱን በማስተባበር መኢገማ ባለው ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በኩል ይህ ነው የማይባል እንቅስቃሴና ገለጻ የሚያደርግ ከመሆኑም ባሻገር በአሉን ቅርንጫፍ በመሥሪያ ቤት አማካኝነት በየክፍለ ሀገሩ ተገቢውን ርብርብ ስለ ሞዓ አንበሳ ምሥረታም ሆነ የውስጥ ደንብ ገለጣ ወደፊት በኛ በኩል መሆን ስለሚገባው ሁሉ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለብን ያረጋግጣል በሚል ጽሁፎችንም በቅርንጫፍ መሥሪያ ቤታችን እናሰራጫለን እናንተም አትለዩን አትዘግዩ ሞዓ አንበሳ ከተኛበት በአንድነት እናንሳው እንቀስቅሰው እንመሥረተው በማለት በከፍተኛ ድምጽ ገልጸዋል የቀኑም ሁኔታ በዚሁ ተደምድሞአል።

በወቅቱ የተፈጠሩ አጋጣሚ ሁኔታ
=====================

በመንበረ ጸባዖት ቤተ ክርስቲያን ዋና በር ደርግ ዘግቶት የነበረው በር በመከፈቱ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ደስታ ማሳደሩ።

ከ17 ዓመታት በኋላ ሕዝቡ ስለሞዓ አንበሳም ሆነ በልዩ ልዩ የፖለቲካ ኃሳብና አስተሳሰብ በፍርኀትና በጥርጣሬ ተውጦ የነበረው ሰፊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውንና የሚሰማውን ከፍተኛ ድጋፍ በይፋ በአንድ ወጥ ከሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካሎች ጋር ኀሳብ ለኀሳብ ሳይፈራ ሳይሸማቀቅ ሳይጠራጠር በመለዋወጥ ዲሞክራቲክ በሆነ መንገድ ለመጀመሪያ ጊዜ የተወያየበት ወቅት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ዝናብ ከገባንበት ቀን አንስቶ ያለማቋረጥ መጣሉ። በወቅቱ የተፈጠረው አጋጣሚዎች ነበሩ።

የወቅቱ የኢትዮጵያ ሁኔታ
================

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባሁኑ ጊዜ በከባድ የኑሮ ችግር ላይ እንደሚገኝ ከመሆኑም ባሻገር ከ4-6 ሺህ የከተማው ነዋሪ ሕዝብ በቤንዚን ማደያ ጣቢያ ለማብሰያ ላምባ ለመግዛት ተራ በመጠባበቅ ለዝናብና ለቁር ተጋልጦ ማየት የሰት ከሰት የሥራ ድርሻ ሆኖአል።

- ለመብል የሚሆኑ እንደጤፍ፣ እንደስንዴ፣ ገብስ የመሳሰሉ ጥራጥሬ ሁሉ ውድ ከመሆኑም ሌላ ከፍተኛ እጥረት ይታይበታል
- እንደሥጋና ቅቤ ዘይት የመሳሰሉት ደግሞ በጣም ውድ ከመሆኑም የተነሳ ሕዝቡ ገዝቶ ለመብላት ያለው የኢኮኖሚ አቅም አነስተኛ በመሆኑ ያለው ብቻ መብላት ይችል ይሆናል በብዛት ያለው ሕዝብ ግን ይህን እድል አያገኝም።
- በከተማው ውስጥ ማታ ከአንድ ሰዓት ጀምሮ በሰዓት እላፊ ምክንያት መዘዋወር አለመቻሉና እንዲሁም ፍተሻ አልፎ አልፎ ስለሚደረግ የከተማ ዓይነት እርጋታና ጸጥታ ከአለመታየቱም ሌላ የአዲስ አበባ ጠቅላላ የከተማው እንቅስቃሴ እንደወትሮው አለመሆኑ፤

በፖለቲካው በኩል
============

አዲስ አበባ ከገባን ጊዜ ጀምሮ ያለውን የቡድኑ መሪ ዶክተር ጌታቸው መካሻ በእንግሊዘኛ ከዚህ ሪፖርት ጋር በማጣጣም የሰጡበት በመሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዞአል።

ጉዞውን በሚመለከት
=============

ጉዞውን በሚመለከት የተደረገውን ወጪ በአጠቃላይ አቶ ለይኩን ብርሃኑ ያደረጉት ከዚህ ሪፖርት ጋር ተያይዞአል።

ወደፊት በአዲስ አበባ
===============

ስሚቋቋመው የሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል ቢሮና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ለመመስረት አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድና ሁለተኛው ዙር የመልእክተኞች ቡድን ወደ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ሄዶ ጅምር ስራውን ማከናወን ቅስቀሳውንና ገለጣውን ማጧጧፍ ይኖርበታል ሕዝቡም በከፍተኛ ተስፋ ይጠባበቃል። በገለጣችንም ጊዜ ሕዝቡ ያሰማው የነበረው መልእክት አትዘግዩ ሥራን በአስቸኳይ ጀምሩ ከአጠገባችሁ ነን የሚል ነበር።

ኢሕአዴግ ያለፈውን ወታደራዊ መንግሥትን የሚደግፉ በግለሰብም ሆነ በድርጅት መልክ ተደራጅተው የሚገኙትን ሁሉ በአሁኑ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ እንዳይካፈሉ በመከልከሉ የተነሳ ለሞዓ አንበሳ ድጋፍ በመስጠት እረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል አባልም ለመሆን በይፋ ጠይቀዋል በዚህም ውስጥ የሚገኙ ምሁራን ወታደራዊ አባሎችና ነጋዴዎች ተማሪዎች የመሳሰለውን የሚያጠቃልል ነበር።

ስለ ልዩ ልዩ የጽሕፈት መሣሪያዎችና እትምት ጉዳይ የሚገልጽ አስተያየት
==

የአባል መመዝገቢያ፣ መዛግብትና ፎርሞች
አርማና አርማ የሌለው ወረቀቶች
የአባል መክፈያ ደረሰኞች ልዩ ልዩ የመሳሰሉትን በፕሮፓጋንዳው መስመር ሊያገለግሉ የሚችሉትን ሥነ ጽሁፎችን ሁሉ እዚህ አሜሪካን አዘጋጅቶ ታትሞ ቢሄድ የተሻለ ይሆናል፣ ምክንያቱም በጥራቱ በኩል የተሻለ ስለሚሆንና በአሁኑ በቅት አዲስ አበባ ውስጥ ይህንን ዓይነት ጽሁፎች ለማሳተም

1ኛ ማተሚያ ቤቶች የሚሰሩት ደርግ ለሴንሰርሽፕ እንዲረዳው ባቋቋመው የእትምት ደንብና ሕግ መሠረት በመሆኑ

2ኛ በቂ የጽህፈትም ሆነ ልዩ ልዩ ማቴሪያል ለማግኘት ስለማይቻል

3ኛ ተራ መጠባበቅ ስለሚኖርበት የመሳሰለውን እንቅፋቶች ስለሚደርሱ እዚህ በቅድሚያ ዝግጅት በማድረግ እንዲጠናቀቅ ቢደረግ የዚህ ሪፖርት አዘጋጆች ያምናሉ።

ተጨማሪ ሃሳብ

==============

ስለ ኃይለ ሥላሴ የሰላምና የእርዳታ ማስተባበሪያ ድርጅት ይህ የእርዳታ ማስተባበሪያ ድርጅት በሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል ጋር ኃይሉን በማስተባበር ከፍተኛ ርብርብ በእርዳታ ማስተባበሪያው በኩል እንዲያደርግ ወቅቱ ይጠይቃል ወይም ማለት እርዳታ ማስተባበሪያው ድርጅት ፖለቲካ መሣሪያ ሆኖ ይሥራ ለማለት ሳይሆን ተጎጂው ህዝብ የሚገኝበትንና የደረሰበትን ችግር የሞዓ አንበሳ አካል ገለጣ በሚያደርግባቸው ክፍለሃገሮችም ሆነ አውራጃዎች በሚዘዋወሩበት ወቅት ችግሩ በተለይ አመዝኖ የት ላይ እንደደረሰ ለማውቅ ስለሚችል በዚህ በኩል የኢንፎርሜሽን መለዋወጥና እርዳታውም ለተጎጂው ሕዝብ መድረስ አለመድረሱን በሚያደርገው የቅስቀሳና የገለጣ ጉዞ ጊዜ ጥናት በመውሰድ ህብረት እንዲፈጥርና እርዳታውም በወቅቱና በጊዜው ለተጎጂው ሕዝብ መድረሱን ጭምር ስብስብ ሪፖርት ማቅረብ እንዲችል ቢደረግ በአንድ ጥይት ሁለት አውሬ እንደመግደል ስለሚሆን በወጪ በኩል ይረዳል ለማለት ነው። ሆኖም እርዳታ ማስተባበሪያው ድርጅት ከፍተኛ የማስተባበር የማቀነባበር በዓለምም ከሚገኘው የእርዳታ ድርጅትና በጎአድራጎት ጋር ያላሰለሰ ግንኙነት በመፍጠር በአሁኑ ጊዜ ከ7 ሚሊዮን ተኩል በላይ ጉዳት ይደርስበታል የተባለውን ወገኖቻችንን ለማትረፍ ጥልቀት ያለው የሥራ ፍሬ ይጠበቅበታል። በመሆኑም በዚህ በኩል የሕዝቡን የወደፊት እድል አብሮ የሚሳተፍ አካል መሆኑንና እንዲሁም ያሁኑ ትውልድ ዓላማውና የጋራ ተልእኮው አገርን የመገንባትና የማሳደግ ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑና ተግባሩም የሚሟላው በሀገራችን ውስጥ ሰላምና ጸጥታ ሲኖር ብቻ ነው። ስለዚህም ድርጅቱ ዓለም አቀፍ እርዳታ በማስገኘት እረገድ ከፍተኛ ተልእኮና አደራ ተጥሎበታል።

በሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አንደኛ ዙር መልእክተኞች በኩል የታየው የአሰራር ድክመቶች

==

1ኛ. በየቀኑ በግል ወይም በቡድን መልክ ያደረግናቸውን ገለጣ ቅስቀሳ ጠቅለል ባለመልኩ ተሰብስበን ወይም ለቡድኑ መሪ ገለጣ ማድረግ አለመልመዳችን፣

2ኛ. ተልእኮአችን በቡድን መልክ እንደሚሰራ መሆኑ እየታወቀ በግል አሰራርና ቅስቀሳ ዝንባሌ መታየቱና በፎቶግራፍ የተጨበጠ ሪከርድ ማስቀረጽ አለመልመዳችን አለመዘጋጀታችን፣

3ኛ. ስብሰባ በምናደርግበት ወቅት የተሰበሰብንበትን ጉዳይ እውሳኔ ላይ ሳንደርስ ወይም እልባት ሳያገኝ በተዝረከረከና በቂ ባልሆነ መንገድ ስብሰባው እንዲቋረጥ ማድረግ፣

4ኛ. ለተነሳንበት ስብሰባ በወቅቱ ለመድረስ አልተቻለም የአየር ትኬቱ አገዛዝ ትክክል አልነበረም ቀላል ወጪ በመፈለግ ወይም ሌላ ሁኔታ ይሆናል ከሦስት ቀን በኋላ ነው አዲስ አበባ ለመድረስ የተቻለው ምክንያቱም የተሰጠን ትኬት

ሀ. ደርሶ መልስ ሲሆን ደርሶ መልሱ የሚያከትመው ኒውዮርክ ላይ ሲሆን እኛ የምንመጣው ግን ዋሽንግተን እንደነበረ ግልጽ ነው

ለ. ቀጥታ ከዋሽንግተን አዲስ አበባ አንድ አየር ብቻ ለውጠን የሚያደርስ ትኬት እያለ ከዋሽንግተን ኒውዮርክ፣ ለንደን፣ወይም ፍራንክፈርት የአየሩን ኮኔክሽን በመፈለግ የሚያዞር ነበር፣ በመሆኑም የማያስፈልግ ወጪ አስከትሏል፤ ይህን ዓይነት የትኬት አገዛዝ ስህተት ወደፊት መቀጠል አይኖርበትም።

5ኛ. ጠቅላላ ባለው ሁኔታ የሞዓ አንበሳ አሰሳሳቢ አካል መመሪያ ቻርተር ደንብ ካለመኖሩም ባሻገር በሥራው ላይ ድክማት ያሳያ በመሆኑና ለድርጅታዊውም አሳራር ችግር እንቅፋት እንደሚፋጥር በሥራው የነበርነው ተገንዝበናል። ስለሆነም በዚህ በኩል የሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል የሥራ መመሪያ የሚሆን ደንብና ህግ ማውጣት እንዳለበት አውቆና ተገንዝቦ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድና ድርጅታዊ አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ የወቅቱ አንገብጋቢ የፖለቲካ ሂደት በማያወላውል ይጠይቃል።

6ኛ. በፕሮግራማችን መሠረት እያንዳንዱ አባል ሥራውን በሥነ ሥርዓት፣ በመከባበር፣ በብልህነት በምክር ከተቀናጀ ግባችንን እንደምንመታ የዚህ ሪፖርት አዘጋጆች ያምናሉ እዚህ ላይ ሪፖርቱን እየደመደምን ከዚህም አማርኛ አጠቃላይ ሪፖርት ጋር፣

ሀ ዶክተር ጌታቸው መካሻ የመልእክተኞች መሪ በእንግሊዘኛ የሰጡት ሪፖርት 6 ገጽ

ለ በጉብኙቱ እንቅስቃሴ ጊዜ ስለተደረገው አጠቃላይ ወጪን በሚመለከት አቶ ለይኩን ብርሃኑ መልእክተኛ የሰጡት ሪፖርት 8 ገጽ ተያይዞ ይገኛል።

ሐ. የዚህ ሪፖርት አዘጋጅ መልእክተኛ ሻ/ገድሉ ኃይሉ የሰጡት ሪፖርት 9 ገጽ በድምሩ 17 ገጽና 6 ገጽ የእንግሊዝኛ ሪፖርት የወቅቱን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካል በኩል የተደረገውን ሂደት ያስረዳል።

የሪፖርቱ አዘጋጅ

=============

ሻምበል ገድሉ ኃይሉ

ዘገባ

===

በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጉባኤ
የቀዳማዊ ዓፄ እምኃ ሥላሴ መልዕክተኞች

========================

የሥራ ክንውን

=========

ይህ የመልዕክተኞች ቡድን ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ በካፒታል ሂልተን ሆቴል የስብሰባ አዳራሽ ግርማዊ ን.ነ.ቀ.ዓፄ አምኃ ሥላሴና ግርማዊት በተገኙበት ቁጥሩ ከሁለት ሺህ በላይ የሆነ ሕዝብ በተሳተፈበት የሞዓ አንበሳ አሰባሳቢ አካልን ህልውና መሥርቶና አሳውቆ ጉዞውን ወደ አዲስ አበባ አመራ።

ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንያቶች ሰኞ ሰኔ 24 ቀን 1983 ዓም (July 1st, 1991) አዲስ አበባ መግባት ሲገባው ጉባዔው በተጀመረ በ4ኛው ቀን አዲስ አበባ ደረሰ። የሞዓ አንበሳ ቡድን (የቀዳማዊ ዓፄ አምኃ ሥላሴ) መልእክተኞች አዲስ አበባ ሲደርስ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቦሌ የዕንግዶች ተቀባይ የፕሮቶኮል ሹም አቶ በትሩ ታየና የኢሕአደግ ተወካይ በልዩ ሳሎን የእንግዳ መቀበያ ቦታ መልዕክተኞችን ተቀብለው አነጋገሩ። የቪዛውና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች እንደተጠናቀቁ ቡድኑ በቀጥታ ወደ ግዮን ሆቴል ጉዞውን አመራ።

ግዮን የመልዕክተኞች ማረፊያና መቆያ ሆኖ የመልዕክቶኞች መምጣት ለሕዝቡና ለባለሥልጣኖቹ ታወቀ። በቦሌ ኤርፖርት የኛ ከዚያ መድረስ የብዙዎች የደስታ ሲቃና ያንዳንዶችም ድንጋጤ ነበር። (በልብሳችን) በኮታችን ደረት ላይ ያንፀባርቅ የነበረው የሞዓ አንበሳ ግርማ የተመልካቾችን ዓይን እጅግ ስቦ ነበር። በተለይም የጃንሆይን ፎቶግራፍ የያዘው የደረት ጌጥ ኤርፖርት ላይ ስናሳያቸው የብዙዎችን ትዝታ ማርኮ ከፊሉ በዕንባ ከፊሉ በዕልልታ ለመቀበል እጇን ዘርግቶ ነበር። ይህ ዓይነቱ ስህበት ጐልቶና ተጠናክሮ የቆየው በግዮን ሆቴል ነበር። ግዮን ሆቴል ውስጥ ከሥራ አስኪያጆች እስከ ሠራተኞች የመልዕክተኞች በዚያ መቆየት ልዩ ጌጥና ድምቀት ሆኖላቸው ነበር። የሠራተኞች አቀባበል ለብዙ ጊዜ ተለይተውት በናፍቆትና በጉጉት የሚጠብቁትን ሰው የማየትና የማግኘት የደስታ መንፈስ ነውጥ ነበር በያንዳንዱ ሰው ፊት ይነበብ የነበረው።

እንኳን ደህና መጣችሁልን!! እንኳን ለአገራችሁ! የሚሉ ድምፆች፣ በዕንባ የተሞሉ ዓይኖች በእንክሮ የተላጉ ፊቶች በየማዕዘኑ ነበሩ። ዕጅ መንሳት፣ ሲፈሩ መሳም አንገት ማቀፍ ማነህ ማን ትሰኛለህን የሚሉት ኃሳቦችና ጥያቄዎችን ጥሰው ይመጡ ነበር እኛም እኛ ነን፤ እናንተም እናንተ ናችሁ፣ ብቻ ነበር የመተዋወቂያው ቋንቋና መግባባት። እውነተኛ መልእክተኞች የምሥራች ነጋሪዎች መሆናችንን ከፊታችን የሚነበብ ለመሆኑ ጥርጣሬ አላሳደረብንም።

ይህ ዓይነቱ አቀባበልና ስሜት በቆየንባቸው ቀናትና ጊዜያት ጨርሰው ያልጠወለጉና ያልተሰለቹ ነበሩ። ይልቁንም የኛ መኖር መታየቱ "አድሮ ዕንግዳ" ነገር ነበር። በመልዕክተኞችም ሆነ በሕዝቡ ዘንድ በቋንቋ የማይገለጽ እንዲሁ በኀሳብ ምህዋር የሚሽከረከር መግባባት ነበረን።

በግዮን ሆቴል ውስጥ የሌሎችም ድርጅቶች ተወካዮች የጉባዔው ተሳታፊዎች አሉ የሚባሉ ታላላቅ ኢትዮጵያውያን መናኻሪያና መጋናኛ (ሬንደቩ.) ሆኖ ነበር። ግዮን ሆቴል ሌላው የጉባዔ ቦታ ነበር። የመልእክተኞች በግዮን መኖር ሕዝቡን እንደ አንድ ትልቅ በዓል ይስበው ነበር። የኛም ሁኔታ የሕዝቡ ጋጋታ መሥመር የተከተለ ውይይት ለማድረግ የሚያስችል መስሎ በሁኔታው ለማረጋገጥ ይከብድ ነበር። ነገር ግን ሕዝቡ እውነተኛ መልዕክት እውነተኛ የምሥራች አዳመጠ፣ መልዕክተኞችን ተመልክቶ፣ ምን ይናገራሉ የሚለውን ጥያቄ ይዞ ኖሯል የተሰበሰበው። በየቄጥራችን አዳማጭ ነበረን። ያለ ፍርሃት ያለ ሁከት ስለሄድንበት ተልእኮ ስለ ጃንሆይ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ አሰማናቸው። የምሥራቹ ድምጽ ጣዕም እንደነበረው ከሰዎች ፊት ፈገግታና ደስታ የተስፋ ሕይወት መገንዘቡ አያዳግትም ነበር።

ይህ ሁኔታ እየተጠናከረና እየበረታ የመጣው ውለን ማደራችንን ባራዘምንባቸው ቀናት ውስጥ ነበር። መልዕክተኛውም ባለው ሁኔታ የሥራ መከፋፈሉን ተግባር ቀጠለ። ከዚህ በኋላ የተለያዩ ክፍሎችን የመልዕክተኞች አባላት ማግኘት ጀመረ። እውነተኛውን የሕዝብ ስሜትና ፍላጎት የለካነው በዚያን ጊዜ ነበር። ቡድኑም ያሉትን የድርጅት ወኪሎች፣ የመልዕክተኞች አባላትን፣ የድርጅት ኃላፊዎችን፣ የውጭ አገር ዜጎችን፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን፤ ኤምባሲዎችን የመንግሥት ባለ ሥልጣኖችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን ሁሉ መልእክተኞች አደረሱ። አነጋገሩ።

ከዚህ ባሻገር የስልክ ጥሪ፣ የሕዝቡ መጉረፍ ቀጠለ። ከጧት እስከ ማታ የሚናስተናገደው ሕዝብ ቁጥር ብዛት በጣም ከፍተኛ ነበር። የመልዕክተኞች ቡድን ለመስተንግዶ የሚመጣውን ሕዝብ ጥያቄ በቃል ብቻ ማስረዳቱ በቂ ሆኖ አላገኘነውም። አንድ መልዕክተኛ በጆሮ የሚሰማ ብቻ ሳይሆን በዕጅም የሚዳሰስ፣ በዓይን የሚታይ ነገር ተፈለገ። በዕውነቱ የመልዕክተኞች ቡድን ይህን ጥያቄ ቀርቦለት ሳይሆን አስፈላጊነቱን አምኖበት የተለያዩ ጽሑፎችን በተለያዩ ኅብረ ቀለማት ወረቀት አዘጋጅቶና ጭኖ አዲስ አበባ ሄዶ ነበር። ነገር ግን በቡድኑ ቦሌ መድረስና በሕዝቡ ስሜት የተደናገጡት የኢሕአደግ ፀጥታ ሹሞች ከዚህ በወሰድናቸው ጽሑፎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት አደረጉና ለምርመራ ይቆዩ ብለው ያዟቸው። የዚያን ሕዝብ የናፍቆት ጥም ያረኩታል ብለን የተዘጋጀንባቸውን ጽሑፎች የሁዋላ በር ዘጉባቸው። እነሱን ለማስወጣት በስምም በመልክም ገና ያልታወቁ አዲስ ባለሥልጣኖች ስም እያቀባበሉን እስከምንመጣ ድረስ ሳናገኛቸው በመቅረታችን የነበረን አማራጭ ለዓይነት በየቦርሳዎቻችን ከያዝናቸው ምንም እንኳን የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ዋጋ ውድ ቢሆንም አባዝቶ መስጠቱን ወሰን። ካረፍንበት ሆቴል በገጽ $2.00 ነበር የሚያስከፍሉት ይሁንና የጽሑፎች መሠራጨት እጅግ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ የተሻለ ዋጋ ማሳተሚያ ፈልገን በገጽ $1.00 እና $0.50 ሂሳብ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጽሑፎችን አባዝተን ተካን። በዚህ ሁኔታ የመጡትን ዕንግዶች ሁሉ በሚታይና በሚዳሰሱ ጽሑፎች አስተናገድናቸው። ጥያቄው፣ ፍላጎቱ የባሰውን ካለን የበጀት አቅም ወጣ። ሆኖም የሚቻለውን ያህል አድርገን ፍላጎቱን አርክትናል ብለን ባናስብም የሚቻለው ሁሉ ተሞክሯል። ምንም እንኩዋን መግለጽና መንገር ባያስፈልግም እኛም አባዝተን ብንሰጥ ይፈቀዳል የሚሉት ጥያቄዎች በመምጣታቸው በደስታ አባዟቸው የሚለውን የሥራ ማቃለያ መልስ ሠጠናቸው። ይሁንና ወደ ጠ/ግዛቶች የሚዳረሱት ላይ ትኩረት አድርገን ከጠበቅነውና ካሰብነው በላይ ወጪ አስከትሎብናል። ሆኖም የሕዝቡን ፍላጎት የኛንም ምኞት በመጠኑ አርክተነዋል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ጋር አብሮ በወቅቱ የተከናወኑት ተግባራት ድጋፍ ሊያደርጉና ለተልዕኮው መሳካት ከፍተኛ ውጤት ያስከትላሉ ብለን ላመንባቸው ያገር ሽማግሌዎች፣ የድርጅት ኃላፊዎች፣ ለሃይማኖት መሪዎች በተለይም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤቶ ክርስቲያን የሲኖዶስ አባላት ከግርማዊነታቸው የተጻፈላቸውን ደብዳቤ አድለናል፣ ከዚያም በመቀጠል ለአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት፣ ለጠ/ግዛት አብያተ ክርስቲያናት በተለይ ለታዋቂ አድባራትና ገዳማት ተመሳሳይ የግርማዊነታቸው መልዕክት ደርሷቸዋል።

የግርማዊነታቸው ልዩ መልዕክት ምን ያህል የኢትዮጵያውያንን ስሜት እንደቀሰቀሰ ባጭር ጊዜ ውስጥ ውጤቱን ለማየት ችለናል። በዚሁ ዓይነት የግርማዊነታቸውን ንግግርም አባዝተን ለሕዝቡ እንዲደርስ በማድረጋችን የአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛው የነዋሪው መወያያና መልካም ምኞት መግለጫ፣ በጐ ምኞት፣ ማጻመጫና መነጋገሪያ ዜና ነበር። "ንጉሥ ሊመጡልን ነው" እግዚአብሔር ሊታረቀን ነው። "እውነት ያድርግልን። " የሕዝቡ የደስታና የተስፋ ምኞት መግለጫ ቃላቶች (ድምፆች) ነበሩ።

የመልዕክተኞች ቡድን በጥቅል ያከናወናቸው ተግባራት ውስጥ ክቡር ቢትወደድ ሡልጣን አሊ ሚራህን ማነጋገር ነበረበት። ክቡር ቢትወደድን በቀጠሮና በአጀንዳ ነበር ሄደን ያወያየነው።

ቢትወደድ ሡልጣን ዓሊ ሚራህ ከረዳቶቻቸው ጋር ሆነው ሂልተን ሆቴል በክፍል ቁጥር 103 ከቀኑ 5.00 ሰዓት ላይ ተቀበሉን። ሲቀበሉን የግርማዊነታቸው ወዳጅና የቤተሰብ ፍቅር እንዳላቸውና እንደነበራቸው መግለጽ ባያሻም ደግመው ራሳቸው የገለጹትና የተናገሩት በመሆኑ አውስቶ ማስፋን አዘጋጁው ይመርጣል።

ከቢትወደድ ጋር ከተወያየንባቸው ፀበይት ጉዳዮች ውስጥ (መካከል) የአፋር ሕዝብ ፍፁም ኢትዮጵያዊ እንደሆነና ከኢትዮያዊነቱም ፍፁምነት የተነሳ በቱርኮች ወረራ ጊዜ ስድስት ሺህ የአፋር ሕዝብ ድንበሩን ሲከላከል እንደሞተ አስረድተውናል። አሁንም አሉ ቢትወደድ "ከዙላ ተራራ እስከ ጂቡቲ" ድረስ የአፋር መሬት ነው። ይህንን ለማንም አይተውም። አይለቅምም። አሰብን ጣሊያን የያዘው በኮንትራት ለወደብ አገልግሎት እንጂ በቅኝ ግዛት አይደለም። አልነበረም የአፋርን ሕዝብና መሬት ከኤርትራ ጋር መደባለቁና የኛ ነው ማለቱ ኤርትራን ነፃ እናወጣለን ብለው ለሚናገሩት ሰዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስረድተናቸዋል። የአፋር ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ነው። ከኢትዮጵያዊነት ፈጽሞ የሚለየው ነገር የለም። ይህንኑም ጉባዔው ላይ በግልጽ አስረድቻለሁ አሉን።

ቀጥለውም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአፋርን ሕዝብ እጅግ አድርገው ይወዱ ነበሩ። የአፋር ሕዝብ እጅግ በጣም የሚወዳቸውና የሚያከብራቸው ነበር። አሁንም የአፋር ሕዝብ በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት የሚያምንና የሚጥር ነው። አንዲት ጠንካራና ብቸኛ ኢትዮጵያ እንድትኖር ነው የሚሻው። እኛም አሉ ቢትወደድ ከቀዳማዊ ዓፄ አምኃ ሥላሴ ጋር ቤተሰብ ነን። ድጋፋችንም ወደ ሁዋላ የማይል ነው። ኢትዮጵያ ከጥንት አገሮች አንዷ ናት አሁንም ያ ሰላማዊው ታሪካዊው የዘውድ መንግሥት መመለስ አለበት። መቸም እግዚአብሔር ለመቅሰፍት ደርግን አስነሳ በእውነቱ ስንመለከተው እኒያ ወታደሮች የጃንሆይን መንግሥት የሚጥሉ አልነበሩም። ግን ሆነ። ያንኑ ያህል ድግሞ እነሆን ከጫካ አስንስቶ ያንን በዘመናዊ ውትድርና የሠለጠነና የታጠቀ ወታደር (ሠራዊት) አጥፍቶና አሸሽቶ እነሆን ከዚህ አደረሰ። ይህም የእግዚአብሔር ኃይልና ታምር እንጂ የነዚህ ሰዎች ኃይልና ችሎታ ሆኖ አይደለም። ይህንኑም ለነመለስ ነግሬያቸዋለሁ። እንደሚገነዘቡትም ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል። በዚህ ዓይነት ውይይቱን ፈጽመን ከ1:30 በሁዋላ ተሰነባበትን።

የኢትዮጵያ ሁኔታ

=============

ኢትዮጵያ ካሉት በታች ከሞቱት በላይ ያለች አገር ሆና ነው የምትታየው። ከዚህ በተሻለ ለመግለጽ ግን "በሞትና በሕይወት" መካከል ላይ ትገኛለች። ሕዝቡ የተስፋ ጭላንጭል ጠፍቶበት፣ የሚያደርገውን አጥቶ ከችሎታ በላይ ብሎ ጩኸቱንና ልቅሶውን፣ ኃዘኑን በቀጥታ አቅርቦ ዝግጁ የሆነ መልስ በመጠባበቅ ላይ ነው። የፀጥታ፣ የሰላም መረጋጋት ገና የረጅም ጊዜ ተስፋ እንጂ ከዕውነት ፈጽሞ የሸሸ እንደሆነ የታወቀ ነው። ሕዝቡ አሁን ምን ይመኛል? ምን ይፈልጋል? ቢባል የመጀመሪያ መልሱ መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ተሟልቶ ማግኘት ብቻ ይሆናል። ሕዝቡ በኑሮው ውድነት ከሚገባው በላይ እጅግ በጣም ተጐሳቁሎ ነው የሚገኘው።

ከዚህም ባሻገር የተረጋጋ ሰላም፣ የሥራ ዋስትና፣ የተረጋጋ ኑሮ ጨርሶ የለም ማለቱ በጥሩ ሁኔታ የሚገልፀው ይመስላል። ምክንያቱም የኑሮው ውድነት፣ የሰላሙ መናጋት፣ የመደበኛ ሥራዎች መታወክ፣ የብዙኃኑ መታሠር፣ በየመንገዱ የሚደረገው ፍተሻ፣ በየቤቱ ያለው ብርበራ፣ መደበኛ የትራንስፖርት መሥመር ያለመቀጠል፣ የት/ቤቶች ያለወቅታቸው መዘጋት፣ ልጆች ያመቱን መደበኛ ትምህርት ሳያጠናቅቁ መቋረጥ። ከዚህም ባሻገር የአብዛኛው የመንግሥት መ/ቤቶች ሥራ መርገብ፣ የሠራተኞች ደሞዝ ያለመክፈል፤ በተለይም የፖሊስ ሠራዊት፣ የጦር ሠራዊትና የሕዝብ ደህንነት ሠራተኞች ከመደበኛ ሥራቸው ጨርሶ መባረር ያገሪቱን የሰላም ይዞት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ጥሎት ይታያል። ከሕዝቡ የኑሮ መቸገር ባሻገር የእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ መደመር የቀኑን መደበኛ ሰዓት በጣም ዝቅ አድርጐታል። ማለት ቀኑን አጨልሞበታል። ጉባኤው በሚካሄድበት ወቅት የኢትዮጵያ ገጽታ ይህን ይመስል ነበር።

የጉባኤው ይዞት ስፋትና ጥልቀት

====================

ጉባዔው ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ባዘጋጀው በኢሕአዴግ ቁጥጥር ሥር የዋለ ነበር። በሕዝብ መገናኛዎች እንደተሰማውና እንደተነበበው ባገሪቱ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ያሉት ድርጅቶች የሚካፈሉበት አልነበረም። ጉባኤው ከአጀንዳ እስከ ውሳኔ ተዘጋጅቶና ተጠርዞ የቀረበ እንኳ ብሉት ተብሎ የተሰጠ ለመሆኑ እስጥ አገባ አያስፈልገውም።

የተጋበዙትም ክፍሎች በድርጅት ስም ሆነ ተብሎ ለድጋፍ ሰጭነት የተኰለኰሉ ነበሩ። የጉባዔውን ይዘትና አቀራረብ የተመለከተ ሁሉ ዲሞክራሲ በስሟ እንጂ በተግባሯ ያልተወከለችበት፣ ጨርሶም ያልታወቀችበት ቦታ ነበር ማለቱ ጥርጥር የለውም።

ይሁንና የሞዓ አንበሳ ተወካዮች በዚህ ዓይነት በተዋቀረው ጉባዔ ላይ አለመገኘት መልካም ነው ቢያሰኝም ያለመሳተፉ ምክንያት ግን ባለው በራሱ ችግር እንጂ በጉባዔው ደዘትና ቅርጽ ሥዕል ያለመፈለግ ተመርጦ አልነበረም። ጉባዔውም እንደ አጀማመሩ ፍጻሜውም ሕዝብን ከሕዝብ፣ አገርን ካገር የሚከፋፍል ሆኖ ነበር የተፈጸመው። ከዚህም ሌላ አንዳንድ ብሔረሰቦች ተወካይ ሆነው የቀረቡት አባላት ለኢሕአዴግ ድጋፍ ሰጭነት እንጂ በእውነቱ በስም የሚጠሩበትን ሕዝብ ወክለው የተገኙ አልነበሩም። እንደተፈራውም የኤርትራን መገንጠል በውሳኔው አስተላለፈ።

ኢሕአዴግ የተቋቋመበት ዓላማ ባይሆንም ቅሉ አዲስ አበባ ሲገባና ኃላፊነት ሲረከብ ዲሞክራሲ የተመላበት ተግባር ለማከናወን የገባውን ቃል የዘነጋው መሆኑ በግልጽ ታይቷል።

ስለሆነም ለሞዓ አንበሳ መልዕክተኞች ያደረገው አቀባበል ቀዝቃዛ ቢሆንም የደረሰበት ችግር ባለመኖሩ መልካም ነበር ማለቱ ተገቢ ይሆናል።

ጉባዔው በተመልካቹ ዘንድ እንደታሰበው እንጂ እንደተነገረለት ሆኖ አልተገኘም። የጉባዔው ታዛቢዎች እንደተናገሩት ለአዘጋጆች ክፍል ብቻ ጥሩ ውጤት ከመሥጠቱ ባሻገር ሌላ ፍሬ አልተለቀመበትም። ሕዝቡ ግን ድሮም ቢሆን ከዚህ ሌላ አልጠበቅንበትም የሚል ድምፅ በየቦታው ነበረው የኤርትራ ጉዳይ የያንዳንዱ የጉባዔው ተሳታፊ ተመልካችና አዳማጭ የሆድ ቁርጠት ነበር ከዚህ ላይ የኤርትራ ጥያቄ ሲነሳ በዚህ ላይ ልዩ አመለካከት የነበራቸውን የጉባዔው ተሳታፊዎች የአፋር ሕዝብ መሪ ቢትወደድ ሡልጣን አሊ ሚራህ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር አሥራት የኦሞቲክና የጉራጌ ተወካይ አስተያየት ሳይወሳ የሚታለፍ አልነበረም። እኒህ አራቱም የኤርትራን ጥያቄ በቀጥታ ትክክል ያለመሆኑን ያሰሙ የጉባዔው አባላት ነበሩ።

ጉባዔው በተሳታፊዎች ብዛትና ድጋፍ ሰጭነት የቀረበው ለኤርትራ ብሔርነት ታጋይ ድርጅት አልፏል። የጉባኤው ኢዲሞክራሲያዊነት ለአንድ ኢትዮጵያ ያለውን ደዞታ በገልጽ ያሳየበት መድረክ ነበር። የጉባዔው ተሳታፊዎች የተመለመሉት ባዘጋጆች ብቸኛ በጐ አስተያየትና ፈቃድ ነበር። ነገር ግን ከዚህ ባሻገር ባገር ውስጥ ተወልደው የጐለበቱና ለደርግ መውደቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ የፖለቲካ ድርጅቶች ከቦታው እንዳይደርሱ የተከለከሉት ቁጥር ጥቂት አልነበረም። ይህም ለዲሞክራሲ ቆመናል የሚመለው የድምፃቸውን ቃና እንደቀየረው ግንዛቤ ተደርጓል።

የወቅቱ ገጠመኝ

ደርግ ጥቅጥቅ አድርጎ በሲሚንቶ የዘጋው የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በር መከፈትና በሥነ ሥርዓቱም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ነፍስ ይማር ከመባሉም በላይ ልጃቸው ቀዳማዊ አምኃ ሥላሴ በኢትየጵያ ያባታቸውን ዙፋን የሚረከቡበት ቀን እጅግ የተቃረበ መሆኑ በግልጽ ተሰብኳል።

ከዚሁ ጋር አብሮ ሊወሳ የሚገባው ጉዳይ ቢኖር ስለ ሞዓ አንበሳ ሕዝቡ ብዙ ለማወቅ እጅግ አድርጎ ፍላጎት ማሳየቱ ነበር። እንዲያውም ለመመዝገብ እንፈልጋለን የሚለው ድምፅ በጥቂቱ የሚቆጠር አልነበረም። ያ ፍላጐት፣ ያ ስሜት እጅግ ጥልቀት ያለው፤ በፍላጎትና በምኞት የተዋጠ ነበር። የሕዝቡ ፍላጎት ከሚታሰበው በላይ መሆኑ መልዕክተኞችን አስደንቋል።

ኢትዮጵያ ታሪኳን ባህሏንና አንድነቷን እንደ ዓይን ብሌን የምትጠብቅበትና አኩሪ ታሪኳን የምታድስበት ቀን በመንጋት ላይ መሆኑ ትንቢት ሳይሆን ገሃዳዊ እውነታ ነው። "ኩሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንኡ"። ሁሉን ሞክሩ የተሻለውን ያዙ። የተባለው ቃል ተግባራዊ የሆነ ይመስላል።

ይህን ዐቢይ ተግባር ለማከናወንና ለመፈጸም ከፍ ያለ የገንዘብ ወጪ ተደርጓል። የመልዕክተኞች መጓጓዣ የዓየር ትኬት ደርሶ መልስ $17,899.82፤ ከጀርመን እስከ አዲስ አበባ ለሆቴልና ለውሎ አበል $29,275.00፤ ለጽሑፍ ማባዣና ለጠ/ግዛት ልዩ ልዩ መልክተኞች የተደረገ ወጪ $12,800.00 እንዲሁም ለልዩ ልዩ ጉዳዮች፣ $8,000.00 በጠቅላላው $67,975.32 ወጪ ተደርጓል።

ማጠቃለያ
======

የመልእክተኞች ቡድን በአዲስ አበባ ከተማ የሰላምና የፍቅር መሠረት ጥሎ ተመልሷል ቢባል በመልእክተኞች ግንዛቤ መሠረት ትክክል ነው። ይሁንና ሥራ ተጀመረ እንጂ ተፈጸመ ስላልሆነ የኢትዮጵያን ብልጽግናና ልማት ለማየት ከልብ ለሚጥሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ታላቅ የምሥራች መሆኑን ከልብ መግለጽ እንወዳለን።

የመልእክተኞች ቡድን ቆይታውን ፈጽሞ የወደፊት ሥራውን አቅዶ ተመልሶ መሠረታዊ ተግባሩን ለመጀመር ወስኖ በሄደበት አኳኋን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ተመልሷል። ቡድኑ በሚመለስበት ጊዜ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ልዩ እንግዳ በመሆን በአንደኛ ማዕረግ ከፍተኛ መስተንግዶ ተደርጐለታል። ይህም ልባዊ የሆነ መስተንግዶ ዘወትር የሚወሳ ነው። የመልዕክተኞች ቡድንም የሄደበትን ተልዕኮ በጥሩ ሁኔታ አከናውኖ ተመልሷል።

በዚህ ሁኔታ ቡድኑም ተመልሶ ኒውዮርክ ከተማ ሲደርስ የአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ድርጅት (The Twelve Tribes of Israel) ራስ ተፈሪያን በጆን ኤፍ ኬኔዲ ኤርፖርት በመገኘት ደማቅ አቀባበል አድርገውለታል። ከዚያም ወደ ድርጅቱ ጽሕፈት ቤት በመሄድ የምሳ ግብዣ ተደርጐለታል ከዚያም በልዩ ቫን ቡድኑ ታጅቦ ጉዞውን ወደ ዋሽንግተን ቀጥሎ ከምሽቱ 11.45 PM ላይ ቨርጂኒያ በሚገኘው የግርማዊነታው መኖሪያ ቤት ደረሰ። በዚህ አኳኋን የመልእክተኞች ታሪካዊ ተልዕኮ ተፈጽሟል።

አዘጋጂና አቅራቢ
ለይኩን ብርሃኑ

አዲስ ዘመን

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ፕሮግራሙን አስተዋወቀ

(ኢ.ዜ.አ) የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ውስጥ የሚንቀሳቀስበትን መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራሙን ባለፈው ሳምንት ለሕዝብ አስተዋወቀ ።

በብሔራዊ ቴአትር ቤት በተካሄደው ስብሰባ ላይ አካሉ የኢትዮጵያ አንድነት ሰላምና ብልጽግና ፣ ዲሞክራሲና ወንድማማችነት እንዲሁም የሀገሪቱ ታሪክ የሚታደስበትን መንገድ የሚሻና የሚያመቻች መሆኑን ገልጿል ።

በቀዳማዊ አምሀ ሥላሴ የበላይ ጠባቂነት በሕገ መንግሥት የተከለለ ስርዓት ሕግ የሚጠብቅና ፈላጭ ቆራጭነትን በማስወገድ እንደብሪታንያና ጃፓን በሥሩ ብዙ ፓርቲዎችን በመያዝ ዘመናዊ ይዘት የሚኖረው ዙፋናዊ አገዛዝ እንዲኖር የሚያደርግ አላማ ያለው መሆኑን በተሰጠው ሰነድ ላይ ተመልክቷል ።

ስብሰባው በቀድሞው የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና አለቃ አያሌው ታምሩ የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ በመሩት ጸሎት የተከፈተ ሲሆን ፣ አፄ አምኃ ሥላሴ ለሽግግር መንግሥቱና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የላኩዋቸው መልእክቶች ተነበዋል ።

በዚሁ መልእክት ለሽግግር መንግሥቱና ለኢሕአዴግ አድናቆታቸውን ከመግለጻቸውም በተጨማሪ ፣ ሰው በላው ሥርዓት በመወገዱ ፣ የተደሰቱ በውጭ ያሉ ናቸው ሰላምን በማስፈን ሀገሪቷን ለመገንባትና በጋራ ለመሥራት ባላቸው ከፍተኛ ፍላጎት የጋራ መድረክ በአስቸኳይ መፈጠር እንዳለበት ተገልጿል።

መልእክቱ [illegible] ኅብረተሰብ ለምርምር ፣ ለልማትና ብልጽግና በሚረባረብበት በአሁኑ ወቅት ጥርጣሬን በማስወገድ በወንድማማችነት መንፈስ ለሥራ መነሳሳት እንደሚገባ ያስረዳል ።

የኤርትራ ሕዝብ የአስተዳደር በደል የደረሰበት ፣ ረሀብና ጦርነት የተፈራረቁበት በመሆኑ ስለ እውነት ለአክራሪነት የተጋለጠ መሆኑ ግልጥ ነው ፣ ቢሆንም አንድነቱ በሰላማዊ እንደሆነም መልእ

(በ7ኛው ገጽ ዞሯል)

የሞዓ አንበሳ . . .

(ከ1ኛው ገጽ የዞረ)

ክቱ ያስረዳል ።

ዶክተር ጌታቸው መኮሻ የሞአ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ሊቀመንበር በአደረጉት ገለፃ ፣ ቀዳማዊ አምሀ ሥላሴ በትረ በእንደሚመጡና የሽግግር መንግሥቱ ሁለንተናዊ ድጋፉን እንዲሰጥ ጠይቀው ፣ የንጉሱ ወደ ሀገራቸው መመለስ የውጭ መንግሥታት በተለይ ምዕራባውያን ለኢትዮጵያ ልማት እርዳታና እገዛ ለማድረግ የሚጠብቁት በመሆኑ ትኩረት ያሻዋል ብለዋል ።

ከዚሁም ሌላ በአረመኔዎች የተገደሉት የአጼ ኃይለ ሥላሴ አጽም ተነስቶ ራሳቸው ባሰሩት በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ መካነ መቃብር በክብር እንዲያርፍ የሽግግር መንግሥቱ መፍቀዱና የበኩሉን ድርሻ ማበርከት እንዳለበት አሰባሳቢው አካል አበክሮ አሳስቧል።



የፕሮግራሙ ትውውቅ ስብሰባ ሲካሄድ ፤

አዲስ ዘመን ኅዳር ፩ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓመተ ምሕረት

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

H.I.M. Amha Selassie I
Emperor of Ethiopia

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የመተዳደሪያ ደንብ

==================================

መግቢያ

====

1. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰሳባሲ አካል መሠረታዊ ዓላማዎችናᎄ ፕሮግራሞችᎄ ለወደፊትም ዕቅዱን በተግባር ለመተርጎም ይቻል ዘንድ ይህ ደንብ የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባባሲ አካል የመተዳደሪያ ደንብ ተብሎ ይጠራል።

2. ለወደፊቱ ለሚከናወኑት ተግባራት ሁሉ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ይህ የመተዳደሪያ ደንብ እየተጠቀሰ መሥራት ይቻላል።

ክፍል 1 የአባላት መብትና ግዴታ

አንቀጽ 1

ሀ/ በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ዓላማ፤ ፕላንና፤ እምነት፤ በውዴታው የተቀበለና ያመነ ሁሉ እንደችሎታው ለድርጅቱ የገንዘብ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤

ለ/ በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምንና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በደል ያልፈጸመ።

ሐ/ አቅሙና አስተሳሰቡ ህሊናዊ ባህሪው ብቁ የሆነ

መ/ በአንቀጹ ተራ ቁጥር የተዘረዘሩትን ካሟላ አባል እንዲሆን ይፈቀድለታል።

አንቀጽ 2

ሀ/ በሞዓ አንበሳም ውስጥ ባሉት የሥራ ኃላፊነት ቦታዎች መምረጥና መመረጥ፤

ለ/ ማንኛውም የሞዓ አንበሳ አባል በዚህ ድርጅት የሚፈጸሙትን መጥፎ ሥራዎች (ሁኔታዎች) ለማሳወቅ ያለውንም ቀሬታ ሁሉ መግለጽ፤

ሐ/ የሥራ አስኪያጅ ቡድን በሚያዘጋጀው ስብሰባዎችና ጉባዔዎች ላይ ይገኛል። ሀሳብ የመስጠት የማፍለቅ የመወከል መብት አለው።

መ/ የድርጅቱ አባሎች በሚሰጡት ማንኛውም ግልጋሎቶች ለመጠቀምና የራሱንም ፖለቲካዊ እምነቶች ለመጠበቅ ይቻላል፤ ነገር ግን ሞዓ አንበሳ እንደሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የተወሳሰቡ የፖለቲካ እምነቶች የሚያራምድ ስለአይደለ ከሞዓ አንበሳ የዲሞክራሲ እምነቶች ውጪ መሥራት ይቻላል ማለት አይደለም።

ሠ/ ማንኛውም የሞዓ አንበሳ አካል የሆነ ሁሉ ሃሳቡንና፤ ቅሬታውን፤ እስከመጨረሻው የሥልጣን አካል ድረስ ማቅረብና ማሠማት ይችላል መልስም የማግኘት መብትም አለው።

አንቀጽ 3

የአባላት ግዴታ

=========

1. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል መተዳደሪያ ደንብን ማክበር

2. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በተግባር መተርጎም

3. እንደአቅሙ አባል የሚከፍለውን መዋጮ ያለማቋረጥ መፈጸም

4. ሞዓ አንበሳ በሚጠይቀው የሥራ መስክ ሁሉ በትጋት መሠማራት መሣተፍ የአባላት ግዴታና ተግባር ነው።

አንቀጽ 4

የሥነ ሥርዓት ጉድለቶች

==============

1. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካላት ነቃፊዎች ጋር መተባበር

2. የተመደቡበትን ሃላፊነት ማጉደል፤ ማበላሸት ሙነትት

3. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ንብረት ማጉደል፤ ማባከን

4. ግዳጅ አለመፈጸም

5. ህዝብን መጉዳትና መጨቆን ወይም [illegible] ተግባሮችን መፈጸም መሥራት

6. ያለበቂ ምክንያት የድርጅቱን መዋጮ ከ3 ወር በላይ ሳይከፍሉ ማቆየት፤

7. ከላይ የተዘረዘሩትን የሥነ ሥርዓት ጉድለቶች የሚፈጽም አባል ካለ የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ ቡድን አካል የዲሲፕሊን ጉባዔ አቋቁሞ እንደጥፋቱ ከባድነትና ቀላልነት ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል።

ክፍል 2

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ቡድን ዝርዝር ተግባራት

=====================================

አንቀጽ 5

1. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የሥራ አስኪያጅ አካላት በሚያወጡት የመመሪያ ዕቅድ፣ ፖሊሲ ለግርማዊነታቸው ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ ተግባራዊ ይሆናል።

2. በአባላቱ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የሥራ አስኪያጅ ቡድን በልዩ ጽ/ቤቱ በኩል ለግርማዊነታቸው ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ በሥራ ላይ ይውላል።

3. የተመረጡት አካላትም እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው ከሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የሥራ አሥኪያጅ ቡድን አካላት ጋር በመመካከርና በመተባበር የዋና ክፍልና የክፍል ሃላፊዎችንና ኮሚቴዎችን ያቋቁማል። ይመርጣል።

4. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ የሥራ አስኪያጅ ቡድን አካላት ኃላፊዎችም የወሰዱት ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ይሆናል ነገር ግን ድምጽ ከመስጠት ደረጃ ከመድረሱ በፊት ውሳኔው በጠቅላላ ስምምነት ቢደርስ የበለጠ ጥሩ ዲሞክራሲያዊ ተግባር ያደርገዋል።

በዚህ ጊዜ ሁሉም ኃሳባቸውን በትክክል እንዲያቀርቡ ዕድል መሰጠት አለበት። በአጠቃላይ በዚህ መልክ ከተዘጋጀ በኋላ ከውሳኔው ጋር ተያይዞ ተመዝግቦ ለመጨረሻ ወሳኝ አካል ይቀርባል።

5. የበታች አካላት ለበላይ አካላት ተጠሪና ተጠያቂ ናቸው።

6. ማንኛውም የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካላት ቡድን ሊወስን ወይም ሊነጋገር የሚችለው ቢያንስ ከአባሎች 2/3ኛ ሲገኝ ነው። በሥራ ጠባያቸውና በአካባቢያቸው ችግር ምክንያት ሊሟላ የማይቻል ከሆነ የበላይ ወይንም ከሥራ አስኪያጅ አካሎች ውስጥ ይህንኑ አስገንዝቦ በአነስተኛ የአባላት ቁጥር ስብሰባው እንዲካሄድ ያደርጋል። ስብሰባም በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ዲሞክራሲያዊ በሆነ ደንብና ሥርዓት ይመራል፤

ክፍል 3

የአመራር አካሎች
===========

አንቀጽ 6

ድርጅቱ 2 ከፍተኛ የአመራር አካሎች ይኖሩታል።

1. ንጉሣዊ ጉባዔ

2. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ የሥራ አስኪያጅ አካላት

አንቀጽ 7

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ጥላ ሥር የተሰበሰቡ አባላት ከ6 ወር ባልበለጠ ከ1 ዓመት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ ስብሳባ እንዲደረግ ስለድርጅቱ ዕድገትና ችግሩንም የሚወያዩበት ጉባዔ ይጠራል።

በየጊዜውም የተፈጸሙ ጉዳዮችን የሚገልጽ ነቂስ ዘገባ ይቀርባል እንዲሁም የድርጅቱ አባላት 2/3ኛ ጠቅላላ ስብሰባ እንዲያደርግ ከጠየቀ ጠቅላላ ስብሰባ በአስቸኳይ ይጠራል

አንቀጽ 8

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ የሥራ አስኪያጅ አካላት

ዘወትር ሥራውን የሚከታተሉና የሚያሠሩ የሥራ ክፍሎች ይመሰርታል ያቋቁማል ።

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የሥራ አስኪያጅ አባሎች በየሥራው ዘርፍ በኃላፊነት የተመደቡትን አባሎችን እንደአስፈላጊነቱ ከቦታ ቦታ ማዛወር ይችላል።

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የሥራ አስኪያጅ አካላት የሚባሉት፤

1. የሞዓ አንበሳ ሊቀ መንበር
2. ም/ሊቃነ መናብርት
3. ጠቅላይ ጸሐፊ ና
4. ዋና ገንዘብ ያዥ ናቸው።

ሀ. የአባላቱን ሥራ አከፋፈልና መቆጣጠሪያ ደንብ ያወጣል

ለ. በሃላፊነት ደረጃ ያለውን የአባሎችን የሥራ ኃላፊነት ይወስናል ይደለድላል ያሻሽላል እንዲቋረጥም ያደርጋል።

ሐ. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ የሥራ አስኪያጅ ቡድን አባላት በዋና ክፍል፤ በክፍል ሹምነት የሚመድባቸውን ሰዎች (በሜሪት ሲስቴም) በጠቅላይ ፀሐፊና በአስተዳደር መምሪያ 3 ካንዲዴቶች እጩዎች ከተመረጡ በኋላ ለሥራ አስኪያጅ ቡድን አባላት ዘንድ ቀርቦ ተወያይተው ከወሰኑ በኋላ በግርማዊነታቸው ይጸድቅና ለተሿሚዎቹ በልዩ ጽ/ ቤት በኩል በይፋ ይነገራቸዋል ደብዳቤም እንዲደርሳቸው ይደረጋል። የሞዓ አንበሳ ጠቅላይ ፀሐፊ ስብሰባ በሚደረግበት ሁሉ የስብሰባውን አጀንዳ ያወጣል፤ ሥራውንም በተሳካና በተቀነባበረ መልክ እንዲከናወን ያልተቆጠበ አገልግሎት ይሰጣል። ለርሱም ም/ዋና ፀሐፊ ይኖረዋል።

ሠ. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ የሥራ አስኪያጅ አባላት ስብሰባ በማድረግ የሞዓ አንበሳ ሊቀ መንበር ለመሆን ከቀረቡት 3 እጩዎች ውስጥ በመምረጥ ለግርማዊነታቸው ቀርቦ ያስወስናል።

ረ. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ የሥራ አስኪያጅ ቡድን አባላት በተለይ ሥራው የሚመለከታቸው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የሥራ ሁኔታ በየ3ቱ ወርና ወይም እንደአስፈላጊነቱ እየተገኘ የተገቢውን ግምገማና ቁጥጥር አስፈላጊም ከሆነ እርማት ይሰጣል። ያደርጋል።

አንቀጽ 9

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የሥራ አስኪያጅ ቡድን በየዓመቱ ወይም በየሁለት ዓመቱ የሚመረጥ የአመራር አካል

ሀ. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የሥራ አስኪያጅ ቡድን በየሥራ ዘፉ ያለውን የሥራ አካል ሁሉ ይመራል ያስተባብራል ይቆጣጠራል።

ለ. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካልን ፕሮግራምና ደንብ በሥራ ይተረጉማል።

ሐ. ለሞዓ አንበሳ የሚያገለግሉ አባሎችን ያሰባስባል።

መ. በተሰጠው የሥራ ሥልጣን ውክልና መሠረት ወጪዎችን ይፈቅዳል።

ሠ. ሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ያለበትን የሃገርና የህዝብ ከፍተኛ ጉዳይና ሃላፊነት በማመን ህዝቡ እየተደራጀ እየነቃ ለሃገሩ እንዲያገለግልና በአንድ ላይም አብሮ ሃገሩ ከወደቀችበት የኤኮኖሚ ውድቀት እንዲያድን ህዝቡን ይቀሰቅሳል ያስተባብራል በተቻለው ሁሉ ይረዳል።

ረ. የአካሉን የፋይናንስ ኮሚቴና የማቴሪያል (ቁሳቁስ) ሁኔታዎችን ይቆጣጠራል ይጠብቃል ያስተባብራል።

ሰ. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አስተዳደር አመራር አካል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ያስተባብራል ይመራል

ሸ. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ ሥራ አስኪያጅ አመራር አካሎች ውስጥ ግርማዊነታቸው ከሚኖሩበት ከተማ ውጪ ለሥራ ከሚሄዱበት ጊዜ በስተቀር ለግል ጉዳይ ወይም በፈቃድ በሚሄዱበት ጊዜ የሥራ አስኪያጅ አባላት አውቀውትና ተረድተው ሥራው እንዳይወዘፍ አስፈላጊውን የሥራ ትብብር ሁሉ እንዲያበረክቱ ያአባላቱ ኃላፊነት ነው።

ቀ. በሞዓ አንበሳ መርሀ ግብር መሠረት የበጀት ረቂቅ ያዘጋጃል። ያጸድቃል።

ሀ. ጽ/ቤቱ የሚገኝበትን ንብረቶች በከፍተኛ በምሥጢር እንዲያዙ እንዲጠበቁ የሥራ አስኪያጅ ቡድን አባላት ኃላፊት ነው።

ለ. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ጽ/ቤት አመቺና አማካይ በሆነ ቦታ እንዲሆንና አባሎችም ከቢሮ ለመገኘት ልዩ ልዩ የትራንስፖርት አገልግሎቶች ለማግኘት በሚያስችል ሥፍራና አካባቢ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት የሥራ አስኪያጅ ቡድን አባላት ልዩ ኃላፊነት ነው።

ጥር 4 ቀን 1984 ዓ/ም

የሥራ መደቡ   የሕዝብ ግንኙነት

የቅርብ ሃላፊው የሥራ መደብ ____________________

የሥራ መደቡ ዋና ዋና ተግባራት

1. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ውስጥ የሚደረገውን የማስተባበር የመቀስቀስ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል ከልዩ ልዩ የሞዓ አንበሳ የሥራ አስኪያጅ አባላት ጋር በመተባበር ከውጪው አካል ጋር ግንኙነት በማድረግ ተጨባጩን የፕሮፓጋንዳ ሚና ይጫወታል።

2. ስብሰባም ሆነ ግብዢያ እንዲሁም ልዩ ልዩ በዓል በሚደረግበትና በሚዘጋጅበት ጊዜ ሁሉ በሚሰጠው ፕሮግራም መሠረት ያስተባብራል።

3. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካላት ስብሰባ በሚያደርጉት ጊዜ ሁሉ አስፈላጊውን መግለጫ> እያዘጋጀ የፕሮግራሙን ቅንጅት በማስፈጸም ሆነ በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች እንዲገለጽ ያደርጋል።

4. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ለቅሳቀስ የሚውሉ ጽሁፎችን ከልዩ ልዩ ፖለቲካዊ የሞዓ አንበሳ አመራር አካላት ጋር በመተባበር የእትምቱ ሥራ በአስቸኳይ እንዲካሄድ ድጋፍ ይሰጣል ሃሳብም ያቀርባል።

5. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ውስጥ ሕዝብ ግንኙነት ሥራ በተሳካና በተቀላጠፈ መንገድ እየተከታተለ የሚሻሻልበትንም ሁኔታ እያጠና ሃሳብ ለሚመለከተው ክፍል ያቀርባል።

6. በሬዲዮ በተሌቪዥን በጋዜጣና በጽሁፍ ሁሉ የሚዘጋጀውን ከሞዓ አንበሳ ዓላማና ግብ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ፖለቲካ አካል ጋር የሚመጣጠን መሆኑን እየገመገመ ለሥራ አስኪያጅ ቡድን አባላት በጠቅላይ ጸሐፊው በኩል እንዲቀርብ ያደርጋል።

7. አባል ምልመላም በኩል በሚደረገው የሥራ ትብብር ከሚመለከተው የሥራ አካል ጋር በመተባበር። ..አፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማል ይረዳል።

8. ጠቅላላ ስብሰባም በሚደረግበት ጊዜ ከጠቅላይ ጸሐፊው ጋር በመተባበር ለስብሰባው የሚሆነውን ቁሳቁስ ሁሉ እንዲሰበሰብ በማድረግ ያልተቆጠበ እርዳታ ያደርጋል።

9. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ውስጥ ያሉት የሥራ ዘርፎች መልካምና ጥሩ የሥራ መግባባት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ጥረትና ቅስቀሳ በማድረግ የሥራ ክፍሉ መልካም የሥራ ትብብርና ግንኙነት እንዲፈጠር ይጥራል።

10. ሌላም ከበላይ የሚታዘዘውን ሁሉ ይሠራል።

የሥራ መደቡ መጠሪያ   ገንዘብ ያዥ

የቅርብ ሃላፊው የሥራ መደብ ___________________

የሥራ መደቡ ዋና ዋና ተግባራት

====================

1. ከልዩ ልዩ ሥፍራ የሚሰጠው የርዳታ ገንዘብ ሁሉ እየተቀበለ በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ያደርጋል።

2. በየወሩ የደሞዝ ክፍያ እንዲደረግ ከአስተዳደር የሚተላለፋትን ዝርዝር መሠረት በማድረግ በቼክ አዘጋጅቶ እንዲፈረመ ያደርጋል።

3. በየጊዜው ከልዩ ልዩ የሥራ አካሎች ተገቢውን መንገድ ፈጽሞ የሚደርሰውን የክፍያ ትዕዛዝ ቸክ እንዲፈርሙ የተወከለቱ ኃላፊዎች መፈረማቸውን ካረጋገጠ በኋላ በቸክ እንዲከፈል ያደርጋል ማንኛውም ክፍያ በቼክ መፈጸም ይኖርበታል።

4, በየቀኑም ሆነ በየጊዜው ከሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካላት የሚከፈለውን የአባልነት ክፍያ፤ የቲ ሸርት ሽያጭ፤ የእስቲከር ሽያጭ ሌላ ሌላም ዓይነት ሽያጭም ሲደረጉ ደረሰኝ እየተቆረጠላቸው ገንዘቡን በየቀኑ በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል በባንክ ቁጥር ገቢ ያደርጋል።

5. መሠረታዊ የሆነው የሂሳብ አሠራር ከተጠናቀቀ በኋላ ወጪን ለመፈጸም የሚቻለው የ´ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ም/ሊቀ መንበር (የአስተዳደር ኃላፊ)ና ሒሳብ ሹሙ ሲፈርሙበት ብቻ ነው።

6. በሁለት የአመራር አካሎች እንዲከፈል በፊርማቸው ከመረጋገጡና ከመፈቀዱ በፊት ግን ስለሂሳቡ ትክክለኝነት የሂሳብ ዋና ሹም በአጭር ፊርማ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

7. ሂሳብ እንዲከፈል በሚደረግበት ጊዜ መጓተት ሳይደረግ በአስቸኳይ እንዲፈጸም ማድረግ የገንዘብ ያዥ ኃላፊነት ነው።

8. ሌላም የበላይ የሚታዘዘውን ይፈጽማል።

የሥራ መደብ መጠሪያ ም/ሊቀ መንበር (የአስተዳደር ዋና ኃላፊ)
የቅርብ ኃላፊው የሥራ መደብ______________________________

የሥራ መደቡ ዋና ዋና ተግባሮች

====================

1. በሥሩ የሚገኙትን የሥራ ክፍሎች ይመራል ያስተባብራል ይቆጣጠራል።

2. አስፈላጊውን የሰው ኃይልና ማቴሪያል ለሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል መሟላቱን ያረጋግጣል እንዲሟላም ያደርጋል።

3. በተሰጠው የሥልጣን ውክልና መሠረት ወጪዎችን ያጸድቃል ይፈቅዳል። ከቦታ ቦታ በሚደረገው ዝውውርና የሥራ ምደባ ተገቢውን ሚና ይጫወታል።

4. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ ድርጅት የሂሳብና ንብረት አያያዝ አጠቃቀም መመሪያ ያወጣል በመመሪያውም መሠረት መፈጸሙን ይቆጣጠራል ይመራል ያስተባብራል።

5. አስፈላጊ የሆኑ የድርጅቱ ልዩ ልዩ የአገልግሎት መሣሪያዎች ቁሳቁሶች ከሥራ ዘርፎች ጋር ግንኙነት እየፈጠረ ሁለእንተናዊ አገልግሎት ያበረክታል እንዲበረከትም ያስተባብራል ይቆጣጠራል።

6. ከየሥራ ዘርፍ በሚቀርብለት የሞዓ አንበሳን የሥራ ፕሮግራም ወጪ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶና አጠቃሎ ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

7. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እየተገኘ የፋይናንስ፤ የአስተዳደር፤ የንብረት ነክ የሆነውን ሥራ ሁሉ ከሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ጠቅላይ ጸሐፊ ጋር በቅንጅት ሆነው በተሰጠው ደንብና ህግ መሠረት መከናወኑን ይቆጣጠራል የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት የየግለሰቦችን ሁኔታ የሚገልጽ ከግል ፋይሎቻቸው ጋር መያያዙን ሁሉ ያረጋግጣል ይቆጣጠራል።

8. በሥሩ ከሚገኙት የሥራ ኃላፊዎች በሚተገዝ የድርጅቱን የዕቃ የቁሳቁስ ልዩ ልዩ ንብረቶች ግዢ ያካሂዳል እንዲካሄድም ያደርጋል ያስተባብራል ይቆጣጠራል፤

9. ሌላም ከበላይ የሚታዘዘውን ሁሉ ይፈጽማል።

የሥራ መደብ መጠሪያ ም/ሊቀ መንበር (የአስተዳደር ዋና ኃላፊ)
የቅርብ ኃላፊው የሥራ መደብ______________________________

የሥራ መደቡ ዋና ዋና ተግባሮች

1. በሥሩ የሚገኙትን የሥራ ክፍሎች ይመራል ያስተባብራል ይቆጣጠራል።

2. አስፈላጊውን የሰው ኃይልና ማቴሪያል ለሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል መሟላቱን ያረጋግጣል እንዲሟላም ያደርጋል።

3. በተሰጠው የሥልጣን ውክልና መሠረት ወጪዎችን ያጸድቃል ይፈቅዳል። ከቦታ ቦታ በሚደረገው ዝውውርና የሥራ ምደባ ተገቢውን ሚና ይጫወታል።

4. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ ድርጅት የሂሳብና ንብረት አያያዝ አጠቃቀም መመሪያ ያወጣል በመመሪያውም መሠረት መፈጸሙን ይቆጣጠራል ይመራል ያስተባብራል።

5. አስፈላጊ የሆኑ የድርጅቱ ልዩ ልዩ የአገልግሎት መሣሪያዎች ቁሳቁሶች ከሥራ ዘርፎች ጋር ግንኙነት እየፈጠረ ሁለንተናዊ አገልግሎት ያበረክታል እንዲበረክትም ያስተባብራል ይቆጣጠራል።

6. ከየሥራ ዘርፍ በሚቀርብለት የሞዓ አንበሳን የሥራ ፕሮግራም ወጪ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶና አጠቃሎ ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

7. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እየተገኘ የፋይናንስ፤ የአስተዳደር፤ የንብረት ነክ የሆነውን ሥራ ሁሉ ከሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ጠቅላይ ጸሐፊ ጋር በቅንጅት ሆነው በተሰጠው ደንብና ህግ መሠረት ለመከናወኑን ይቆጣጠራል የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት የየግለሰቦችን ሁኔታ የሚገልጽ ከግል ፋይሎቻቸው ጋር መያዙን ሁሉ ያረጋግጣል ይቆጣጠራል።

8. በሥሩ ከሚገኙት የሥራ ኃላፊዎች በመገናዘብ የድርጅቱን የዕቃ የቁሳቁስ ልዩ ልዩ ንብረቶች ግዢ ያካሂዳል እንዲካሄድም ያደርጋል ያስተባብራል ይቆጣጠራል።

9. ሌላም ከበላይ የሚታዘዘውን ሁሉ ይፈጽማል።

የሥራ መደቡ መጠሪያ ጠቅላይ ጸሐፊ

የቅርብ ሃላፊው የሥራ መደብ ______________________

የሥራ መደቡና ዋና ዋና ተግባራት

======================

1. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ውስጥ በሚደረገው ስብሰባ አጀንዳ ይይዛል፤ ቃለ ጉባኤ በጥንቃቄ ይመዘጋባል ወሳኔዎችንም በአጠቃላይ አቅርቦ በየመልካቸው እንዲፈጸሙ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማል ያስፈጽማል።

2. የአባል ምልመላዎችን በተሰጠው ደንብ መሠረት ያከናውናል ።

3. የአባል መታወቂያ ደብተር ከሚመለከተው የሥራ ክፍል ጋር በመተባበር እንዲታተምና ለሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል አባሎች የሚገባውን ክፍያ መፈጸም አለመፈጸማቸውን ይቆጣጠራል ያስፈጽማል።

በተሰጠው ደንብና ህግ ቻርት መሠረት የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሥራቸውን ማካሄዳቸውን ይቆጣጠራል ቁጥጥሩም ከአስተዳደር አመራር ጋር የተቀናጀ ይሆናል።

5. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ግብዣ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ከአስተዳደርና ከሕዝብ ግንኙነት ተጠሪ ጋር በመተባበር ተፈላጊውን አስተዋጽኦና የሥራ ክንውን በቅንጅትና በጥሪው በኩልም ስለሚደረገው ተገቢውን የሥራ ትብብር ይፈጽማል።

6. በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ጽ/ቤት በኩል ስለሚደረገው የሥራ ክንውን አስፈላጊውን ያበረክታል ይፈጽማል ያስፈጽማል ይቆጣጠራል።

7. በየወሩ የሥራውን እንቅስቃሴ እየገመገመ አስፈላጊውን እስታቲስቲካዊ ዶኪመንቶች ይይዛል። ለሥራ አስኪያጅ ቡድን አባላትም እንዲቀርብ ያደርጋል።

8. ከሥራ አስኪያጅ አባላት ጋር በመተባበር በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል አባላት ውስጥ ከቦታ ወደ ቦታ በሚደረገው የዝውውር ውድም የሥራ ድልድል ከፍተኛውን ሚና ይጫውታል።

9. በየጊዜው የተፈጸመና ያልተፈጸመም ጉዳዮች የሚገልጽ ነቂስ ዘገባ በየ3ቱ ወር የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም ሆነ ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴዎች እንዲቀርብ ከዚያም አጠቃሎ ለበላይ እንዲቀርብ ያደርጋል

10. ማንኛውም የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የሆነ ሁሉ ሃሳቡንና፣ ቅሬታውን፣ እስከመጨረሻው የሥልጣን አካል ድረስ ለማቅረብ በሚያደርገው እንቅስቃሴ አባሎችን ይረዳል ይከታተላል መልስም ለማስገኘት በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ የሚመለከታቸው የሥራ አካል በማስተባበር ያስፈጽማል ይፈጽማል።

11. በልዩ ልዩ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ውስጥ ስለሚደረገው ስብሰባ ጉዳይ ሁሉ በቃለ ጉባኤ አመዘጋገብ በኩል ስላለው ሁኔታ ያመቻቻል።

12. ሌላም ከበላይ የሚታዘዘውን ሥራ ይሠራል።

የሥራ መደቡ ዋና ዋና ተግባራት

1. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የሥራ አስኪያጅ አባላትን በሊቀ መንበርነት ይመራል።

2. ከግርማዊነታቸው የሚሰጠውንና የተሰጠውን መመሪያ በመከተል ም/ሊቀ መናብርትና ጠ/ጸሐፊ እየተረዳ የሥራ አስኪያጅ አባላትን ያስተባብራል።

3. የፖለቲካ መግለጫዎችን እንደአስፈላጊነቱ እያጠና እየተከታተለ ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴዎች ጋር በመተባበር በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ስም መግለጫዎችን ያወጣል። እንዲወጣም ያስደርጋል።

4. የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ኮንስቲቱዩሽናል ሞናርክ ዓላማን ግብ ለማምታት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ለሐገርም ውስጥ ሆነ ለውጭ አገር ጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይሰጣል።

5. ግርማዊነታቸው በሚገኙበት በማንኛውም ስብሰባ ላይ የሚነገረውን ዲስኩርና ሌላም ከሥራ አስኪያጆቱ አባላትን በማስተባበር ለወቅቱ ተገቢ የሆነ ዲስኩር ያዘጋጃል እንዲነበብም ያደርጋል።

6. ፖለቲካውን በቅርብ እየተከታተለ ከዓለም የፖለቲካ አካል ሁኔታ ጋር ያስተባብራል ያዛምዳል ተለዋጭም ሁኔታ ከተፈጠረ የድርጅቱን የሥራ አስኪያጅ አባላት በማሰባሰብ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል።

7. ከኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ወይም ጊዜያዊ መንግሥት ወይም ልዩ ልዩ ድርጅቶች ጋር በሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ የሥራ አስኪያጅ አባላት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ተገቢውን ግንኙነት ይፈጥራል ያስተባብራል።

8. በተቻለ መጠን በየጊዜው የተደረጉትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሶሻል፤ እንቅስቃሶ ለውጦችን ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴዎች ጋር በመተባበር ግምገማና ፕላን በማድረግ ተገቢው ይፈጽማል ያስፈጽማል ያስተባብራል።

9. ለድርጅቱ ሥራ እንቅስቃሴ ወጭ የሚውለውን የደሞዝ፤ የልዩ ልዩ ወጪ የዓመቱ በሚቀርብለት ዝርዝር መሠረት የሥራ አስኪያጅ ቡድኖችን በማሰባሰብ ሁኔታውን በጋ በኋላ ይወስኑና ለግርማዊነታቸው በልዩ ጽ/ቤታቸው በኩል ቀርቦ እንዲፈቀድ ያደርጋል

10. ለድርጅቱ የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ እርዳታ የሚገኝበትን ሁሉ እየተከታተለ እንዲ ያደርጋል ይረዳል ያስተባብራል።

11. ከግርማዊነታቸው ሌላም የሚታዘዘውን ሁሉ ይፈጽማል

ሞዓ አንበሳ
'MO-ANBESSA'
ዘውዳዊ አስባሳቢ አካል
THE CONQUERING LION
ETHIOPIANS FOR CONSTITUTIONAL MONARCHY

ለክ____

____

____

ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን

ትውልድ ያልፋል ትውልድ ይተካል ዛሬ ወደ ትላንት ነገ ወደ ዛሬ ይተሳሰፋል። ሕይወት ፍጥነቱን ይህ ነው በማይሉት ምሕዋር ያሽከረክራል። ይሁንና እያንዳንዱ ዜጋ ለቤተሰቡና ለሀገሩ አንድ ተጨባጭ የሚታይና የሚዳሰስ ቅርስ ወይንም ተግባር ሠርቶ ማለፍ ብሔራዊ ዜጋዊ የግዴታ ግዴታ መሆኑን ማወቅ መገንዘብና ማስተዋል እንደሚገባ እውን ነው።

ያገር አንድነት፣ ያገር መበልጸግ፣ ያገር መልማት ኩራቱና ጥቅሙ ለዜጎች ሁሉ መሆኑን እንረዳለን ስለሆነም በኢትዮጵያ ውስጥ ፍፁም ሰላም፣ ፍቅርና አንድነት፣ ዕኩልነትና ወንድማማችነት ይቅር ተባባይነት ሠፍኖ ለአገርና ለወገን ጥቅም በሚሰጥና በሚያደርግ ተግባር ላይ የሚተኮርበት ወቅት ቢኖር ይህ ጊዜ ነው።

የዓለም ሕዝብ ለፈጠራ፣ ለልማት፣ ለብልፅግና በሚሮሯጥበት ወቅት ርስ በርስ መዋጋት፣ ርስ በርስ መጻማማት በተግባር ሊያዩት ይቅርና ሊሰሙትም እጅግ የሚዘገንን ነው። ይሁንና ይህ ድርጊት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታይ የመድረክ ትርዒት ነው። ታዲያ ይህን መሳዩን መቅሰፍት፣ ችነፈር፣ ኃዘን ዋይታና ልቅሶ የማንሰማበት፣ የማናነብበትና የማናወራበት ጊዜው መቼ ይሆን?

ፍፁም ወዳጆቻችን ሆይ!

በተለይ በዚህ በእንግድነት በምንኖርበት አገር ውስጥ በግል ጥረታችሁና ግረታችሁ ድርጅት መሥርታችሁ ኢትዮጵያውያንን ወገኖቻችሁን በፈጠራችሁት ሥራ ተካፋይ አድርጋችሁ ራሳችሁን ችላችሁ በሥራችሁ ተግታችሁ ማየቱ ምን ያህል የኀሊና ደስታ እንደሚሰጥ በቀላሉ የሚገልጹት አይደለም።

P.O. BOX 38,OAKTON, VIRGINIA, 22124, TEL. NO. (703) 264-0197

ይህን ጥንካሬያችሁን፣ ብርታታችሁን ኢትዮጵያን ለማልማት እንዲውል እንደምታስቡ ገሀድ ነው ግን ይህን ለማመቻቸት አንድነት ሰላምና ፍቅር እንዲጠነክር ለማድረግ ሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል እጅግ ልባዊ ጥረት ያደርጋል። ታዲያ የያንዳንዳችንን ድጋፍና ተሳትፎ እጅግ አድርጐ በጥብቅ ይሻል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ውበት የዓለምን ሕዝብ እንደማረከች ናት። በተፈጥሮ ኃብቷም እጅግ የበለፀገች ናት ነገር ግን ገና አለማችም። ይህ ትውልድ ይህን የማድረግ ግዴታ እንዳለበት በጽኑ እናምናለን። ይህን ለማስፈፀም ጥረት ላይ ነን። እናንተም የመሳተፍ፣ የመሥራት፣ የማብልፀግ ኃላፊነታችሁን ከተገነዘባችሁት ውሎ አድሯል። ነገር ግን ምኞትን በተግባር ለመተርጐም ቀላል እንዳልሆነ የምትገነዘቡት ነው። ይሁንና ከልብ ከጣሩ፣ ከልብ ከሠሩ የማይሆን ከቶ ምን ነገር አለ? በተለይም ይህን ሸውታና ውሸንፍር የበዛበትን ወቅት በጥላነት፣ በመጠጊያነት የሚያገለግለን በሕግ የተወሰነ ዙፋናዊ መንግሥት ስንዘረጋ እንደሆነ ነው። ይህም አማራጭ የማይገኝለት ብቸኛ ታሪካዊና ባህላዊ መመኪያችን ነው።

የኢትዮጵያ አንድነት ተጠብቆ የኖረውም ስለዚሁ ነው። ስለሆነም ለአገር ምን የማይሆንላት ነገር አለ? አባቶች ለአገራቸውና ለሕዝባቸው እንኳንስ ንብረታቸውን ሕይወታቸውን ሠጥተዋል። ስለ አገራቸው ፍቅር ሞተዋል፤ ተገድለዋል። ተርበዋል ተጠምተዋል፣ ተሰደዋል። ስደት ቱሪዝም አይደለም። አካባቢን ዘመድ አዝማድን ጥሎ ባህሉ ከባህሉ፣ ቋንቋው ከቋንቋው፣ መልኩ ከመልኩ ከማይዛመድበትና ከማይመሳሰልበት አካባቢ ለመኖር መገደድ ያለውን ችግር፤ ውጣውረድ ምን ያህል እንደሆነ ሁላችንም የምናውቀው የዓይን ምሥክሮች ነን።

ወዳጆቻችን ሆይ!

ይህን የመሰለው ሕይወት በዚሁ መልኩ እንዲቀጥል ፈፅሞ አንሻም። ከዚህ ላይ ልናስገነዝበው የምንሻው አንዱ አሳዳጅ ሌላው ተሰዳጅ የሚያደርገውን አምባገነንነትና ማን አህሎኝነት በጠቅላላው ዓረመኒያዊነት ከሥሩ መንግለን ከእሳት መጣል አለበለዚያም ከባህር መጨመር ነው።

አገር ካለች ክብር አለ። ወገን ካለ መተባበር፣ መፈቃቀር አለ። በባዕድ ባህል፣ በባዕድ ሥርዓት አንገታችንን አንቀን መሞቱ ይብቃ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ባለው ችሎታና ዕውቀት ተሠማርቶ አገሩን አልሚና አበልፃጊ መሆን አለበት። ያካበተውን ዕውቀት፣ ንብረትና የኑሮ ፈሊጥ ሁሉ በአገሩ ሕዝብና መሬት ላይ ሄዶ ማሳረፍ፣ ማብርከት አለበት እንላለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ በጣም አጥቶና ነጥቶ የሚታየው በሰላም እጦት ነው። ሰላም ካለ ፍቀር አለ። ፍቅር ካለ አንድነት አለ። በጋራ የማይሠራ፣ የማይመረት፣ የማይከናወን ከቶ ምን አለ? የኢትዮጵያ ታሪክ እንደ ዕንቁ የሚያብረቀርቀው በዜጐቿ አንድነትና ጥንካሬ የተገነባና የተመሠረተ በመሆኑ ነው።

ስለዚህ ሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል የኢትዮጵያን አንድነት፣ ሰላምና ወንድማማችነት ለማጠናከርና በተግባር ለመግለጽ ሌት ከቀን በጥረት ላይ ነው። ዓላማውም ኢትዮጵያን እንደ ሲሚንቶ አንድ አድርጐ የሚይዘው ታሪካዊው ዙፋናዊ መንግሥት ሲመሠረት መሆኑን በጽኑ ያምናል። ስለዚህ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የርስዎን ተሳትፎ እጅግ አድርጐ ይፈልጋል። ኢትዮጵያ በሕይወትና በሞት መካከል ላይ ትገኛለች። እርስዎ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ የኢትዮጵያን ኀልውና የሚያድን መድኃኒት ነውና አሁንኑ የሚችሉትን ይለግሱ። ለዚህ ሥራ ተካፋይ ይሁኑ። ይህም የዜግነት፣ የብሔራዊ ግዴታዎ መሆኑን ይገንዘቡት።

ለሚለግሡት ስጦታ ሁሉ ሕጋዊ ደረሰኞች አሉን የምሥጋናም ደብዳቤ ይከተላል። ስለ ትብብርዎና ስለ መልካም ተግባርዎ ምሥጋናችንን እያቀረብን ርዳታዎን በጉጉት እንጠብቃለን።

የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል
የሥራ አስፈጻሚ ክፍል

አድራሻችን
ሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል
የመ.ሣ.ቁጥር 38
Oakton, VA 22124

Phone (703)264-0197
FAX (703)758-0816

ግርማዊ ቀዳማዊ አምሃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
H.I.M. Amha Selassie I
Emperor of Ethiopia

ሰኔ 21 ቀን 1983ዓ.ም.

ለ ________________________

____

ከሁሉ አስቀድመን አገራችንንና ሕዝባችንን ከረሀብ ፣ ከጦርነትና ከመከራ አውጥቶ ሰላም ፍቅርና አንድነት ይሰጥልን ዘንድ ሁሉን ለማድረግ ለማይሳነው ፣ ለኃያሉ እግዚአብሔር ያልተቋረጠ ልመናችንንና ጸሎታችንን እናሰማ ::

ስለሆነም በአገር ሽማግሌነት ስለ አገራችን ደህንነት ሕዝቡን በማስተባበርና በማረጋጋት ከፍተኛ ጥረት እንድታደርግ ከፍተኛ አደራ ተጥሎብሃል ::

ከኛ ጋርም በዓይነ ሥጋ የምንተያይበት ሩቅ እንደማይሆን እናሳስባለን ::

ለሁሉም ኃያሉ እግዚአብሔር ይርዳን ::

የቀዳማዊ አምኃ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ጽ/ቤት

ቅጽ ሐ-00

የገንዘብ መክፈያ ደረሰኝ

=================

የተቀባይ ስም: ____________________

የሥራ ክፍል: ____________________

የተከፈለበት ምክንያት: ____________________

____

የገንዘቡ ልክ በአሃዝ $________ ________

በፊደል: ____________________

____________________ ____________________

ፊርማ ቀን

____

የሂሳብ ሹም ፊርማ